# <u>የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ሥልጣን ፡ በመወሰን ፡ ረገድ ፡</u>
## <u>ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ስላለው ፡ መብት ፡፡*</u>

ከአበራ ፡ ጀምበሬ (ቢ ፡ ኤ ፤ ኤል ፡ ኤል ፡ ቢ፡)**

*"ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ የሚሠራባቸውን ፡ የመሥሪያ ፡ ቤቶችንና ፡ የሚኒስቴሮችን ፡ ሁሉ ፡ የሥራ ፡ አኳኋን ፡ አቋቁሞ ፡ ይወስናል ፤---"*

*የተሻሻለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡*

## <u>መግቢያ ፦</u>

በዚህ ፡ የምርምር ፡ ድርሰት ፡ ውስጥ ፡ "የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡" የሚለው ፡ ስያሜ ፡ የሚያመለክተው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ትእዛዝ ፤[1] በመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡[2] ወይም ፡ በሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፤[3] ከአንድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ ቅርንጫፍ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ ከሕግ ፡ አውጭው ፡ ክፍል ፡ በቀጥታ ፡ ሳይያያዙ ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ እንዲተዳደሩ ፡ የሚቋቋሙ ፡ የመንግሥት ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ ክፍሎችን ፡ ነው ፡፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚቋቋሙ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ቦርድ ፤[4] ባለሥልጣን ፤[5] ጽሕፈት ፡ ቤት ፤[6] ኮሚሽን ፡ (ኮሚሲዮን) ፤[7] ማዘጋጃ ፡ ቤት ፤[8] አስተዳደር ፤[9] ኮርፖሬሽን ፤[10] ኮሚቴ ፤[11] ኢንስቲትዩት ፤[12] ድርጅት ፤[13] ወይም ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፤[14] በመባል ፡ በተለያየ ፡ ስም ፡ ይጠራሉ ፡፡

---

* ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ በመጀመሪያ ፡ ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፤ ለመጨረሻ ፡ ዓመት ፡ ሰሚናር ፡ የቀረበ ፡ ጥናት ፡ ነበር ፡፡ በኋላም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ ለማሳተም ፡ በሚስማማ ፡ አኳኋን ፡ ተሻሽሏል ፡፡

** በምክትል ፡ ሚኒስትር ፡ ማዕርግ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ዋና ፡ ጸሐፊ ፡፡

1. የሲቪል ፡ አቪያሲዮን ፡ ትእዛዝ ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፭ ፤ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ <u>ነጋሪት ፡ ጋዜጣ</u> ፤ ቁጥር ፡ ፲፯ ፤
2. የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፶፱ ፤ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ <u>ነጋሪት ፡ ጋዜጣ</u> ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡፡
3. የመንግሥት ፡ አገልግሎት ፡ ጡረታ ፡ ጉባዔ ፡ ቻርተር ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፶ ፡ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ <u>ነጋሪት ፡ ጋዜጣ</u> ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡፡
4. የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ ፡፡
5. የኢትዮጵያ ፡ መብራትና ፡ ኃይል ፡ ባለሥልጣን ፡፡
6. ጠቅላይ ፡ ፖስታ ፡ ቤት ፡፡
7. የመንግሥት ፡ አገልግሎት ፡ ጡረታ ፡ ጉባዔ ፡፡
8. የአዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡፡
9. የኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊ ፡ ታሪካዊ ፡ ቅርሶች ፡ አስተዳደር ፡፡
10. የኢትዮጵያ ፡ የእህል ፡ ማኅበር ፡፡
11. የልማት ፡ ሥራ ፡ ለማስፋፋት ፡ የተቋቋመ ፡ ኮሚቴ ፡፡
12. የእርሻ ፡ ምርምር ፡ ኢንስቲትዩት ፡፡
13. የኢትዮጵያ ፡ ቱሪስት ፡ ድርጅት ፡፡
14. የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡፡

የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሕግ ፡ አስፈጻሚውን ፡ የሕግ ፡ አውጭውንና ፡ የዳኝነት ፡ ክፍልን ፡ የሚመስል ፡ ሥልጣን ፡ ማኅደር ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ እንደአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ በማስተዳደር ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ አውጭው ፡ ክፍል፡ ሕግ ፡ በማውጣት ፡ እንደዳኝነቱ ፡ ክፍል ፡ ፍርድ ፡ በመስጠት ፡ የግለ - ሰቡን ፡ መብት ፡ የሚነካ ፡ ተግባር ፡ ያከናውናሉ ።[15]

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚከተሉትን ፡ ጥያቄዎች ፡ እንመረምራለን ፡

አንድ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚቋቋምበት ፡ ሕግ ፡ በምን ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ መውጣት ፡ አለበት ? የሕጉስ ፡ ዓይነት ፡ (ፎርም) ፡ ምን ፡ መሆን ፡ አለበት ? በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ መሠረት ፡ በታወጀ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሊሰጥ፡ የሚችለው ፡ ሥልጣን ፡ ስፋት ፡ እስከምን ፡ ድረስ ፡ ነው ? የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ በመመርኰዝ ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሊሰጥ ፡ የሚቻለው ፡ ሥልጣን ፡ የአስፈጻሚውን ፡ የሕግ ፡ አውጭውን ፡ ወይም ፡ የዳኝነቱን ፡ ክፍል ፡ ሥልጣን ፡ የሚመስል ፡ ሊሆን ፡ ይችላልን ?

እነዚህን ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ጥያቄዎች ፡ ለመመለስ ፡ የአንቀጹ ፡ ደራሲ ፡ (፩ኛ) ፡ በትእዛዝ ፡ አማካይነት ፡ ሊሰጡ ፡ የሚችሉትን ፡ ሥልጣኖች ፡ በአዋጅ ፡ ወይም፡ በድንጋጌ ፡ ሊሰጡ ፡ ከሚችሉት ፡ ሥልጣኖች ፡ ለመለየትና ፡ (፪ኛ) ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ሥልጣን ፡ በመወሰን ፡ ረገድ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የተጠበቀውን ፡ መብት ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ከተበጀለት ፡ ገደብ ፡ ጋር ፡ አዛምዶ ፡ ለማሳየት ፡ ይሞክራል ።

ይህንንም ፡ ለማድረግ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕጋዊ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ያላቸውን ፡ የእድገት ፡ እርምጃዎች ፡ እና ፡ እጅግ ፡ የተለያየ ፡ መልክ ፡ ያላቸውን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ሥልጣኖች ፡ እንመረምራለን ። በተጨማሪም ፡ በአስተዳደሩ ፡ ክፍል፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ የሚሰጥባቸውን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴዎች ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ እንደምን ፡ እንደሚወስናቸው ፡ እንመለከታለን ። ሆኖም ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ሕገ መንግሥት ፡ የተደረሱ ፡ በቂ ፡ ጽሑፎችና ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ የሚመለከቱ ፡ ብዙ ፡ የፍርድ ፡ ጉዳዮች ፡ ባለመኖራቸው ፤ ምርምራችን ፡ በጣም ፡ የጠለቀ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም።

ደራሲው ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ሊሠነዝር ፡ የሚሞክረው ፡ ዋና ፡ ሀሳብ ፡ እንደሚከተለው ፡ ባጭሩ ፡ ሊገለጥ ፡ ይችላል ።

ሀ/ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ በመመርኰዝ ፡ አንድን ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ለማቋቋም ፡ ተግባሩን ፡ ለመወሰንና ፡ ከመቆጣጠር ፡ ከፖሊስ - መሰል ፡ እና ፡ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ነክ ፡ ጉዳዮችን ፡ ከሚመለከት ፡ የመቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፡ በስተቀር ፡ ማንኛውንም ፡ ሥልጣን ፡ ለመስጠት ፡ ይቻላል ።

ለ/ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚሰጥ ፡ የመቆጣጠር ፡ የፖሊስ ፡ መሰል ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ነክ ፡ ጉዳዮችን ፡ የሚመለከት ፡ የመቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዲኖረው ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፬ ፡

15. በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ተግባራቸውን ፡ በማከናወን ፡ ውሳኔ ፡ ሲሰጡ ፡ ደንብ ፡ ሲያወጡ ፡ እና ፡ ተመሳሳይ ፡ እርምጃዎችን ፡ ሲወስዱ ፡ የሚከተሉትን ፡ የአስተዳደሩን ፡ ክፍል ፡ ሥርዓትም ፡ ሆነ ፡ ሥልጣናቸውን ፡ የሥራ ፡ አመራራቸውንና ፡ ውሳኔያቸው ፡ በፍርድ ፡ እንደገና ፡ የሚታይበትን ፡ ሁኔታ ፡ የሚወስነውን ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ሕግ ፡ አንመረምርም ።

እና ፡ ፹፰ ፡ መሠረት ፡ በወጣ ፡ አዋጅ ፡ ወይም ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ መሠረት ፡ የፓርላማ ፡ መማክርት ፡ ባልተሰበሰቡበት ፡ ጊዜ ፡ የሚያስቸኩል ፡ ጉዳይ ፡ ተገኝቶ ፡ በወጣና ፡ መማክርቱ ፡ በሚሰበሰቡበትም ፡ ጊዜ ፡ ቀርቦ ፡ እንዲጸድቅ ፡ በሚደረግ ፡ ድንጋጌ ፡ መደገፍ ፡ አለበት ።

ሐ/ በአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ መሠረት ፡ የወጣ ፡ ትእዛዝ ፡ ለአንድ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የመቆጣጠር ፡ የፖሊስ ፡ መሰል ፡ ወይም ፡ የመንግሥቱ ፡ ገንዘብ ፡ ነክ ፡ ጉዳዮችን ፡ የሚመለከት ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቶ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ሊኖረው ፡ የሚችለው ፡ አግባብ ፡ ባለው ፡ አዋጅ ፡ ወይም ፡ ድንጋጌ ፡ የተደገፈ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

በአዋጅ ፡ ወይም ፡ በድንጋጌ ፡ መልክ ፡ የወጣ ፡ ደጋፊ ፡ ሕግ ፡ ሳያስፈልግ ፡ በአንቀጽ፡ ፳፯ ፡ ብቻ ፡ ላንድ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ሊሰጥ ፡ መቻል ፡ አለመቻሉን ፡ ለመወሰን ፡ የሚያስችል ፡ መመሪያ ፡ ካዘጋጀን ፡ በኋላ ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለተሰጡት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥልጣኖች ፡ የተለየ ፡ ጥናት ፡ እናደርጋለን ። የተለየውም ፡ ጥናት ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ የተሠነዘረውን ፡ የደራሲውን ፡ ሀሳብ ፡ በተጨበጠ ፡ ምሳሌ ፡ ለማብራራት ፡ ነው ። የደራሲውን ፡ ሀሳብ ፡ የተቀበለ ፡ እንደሚገነዘበው ፡ ሁሉ ፤ በአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱት ፡ ጥቂት ፡ ቁጥሮች ፡ በቀጥታ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ሲኖራቸው ፡ አንዳንዶቹ ፡ ግን፡ ያለተጨማሪ ፡ ሕጋዊ ፡ ድጋፍ ፡ ተፈጻሚነት ፡ አይኖራቸውም ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## ጠቅላላ ፡ ምርመራ ።

## ምዕራፍ፡ ፩ ።

## ስለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መብት ።

### ሀ/ ታሪካዊ ፡ መግለጫ ።

የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መብት ፡ አመጣጥ ፡ እና ፡ የመሻሻል ፡ ሁኔታ ፡ መመርመር ፡ ይቻለን ፡ ዘንድ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድመን ፡ ስለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መብት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕጋዊ ፡ ታሪክ ፡ እንመለከታለን ። ለዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ዓላማ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ እድገት ፡ ታሪክ ፡ በሦስት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ክፍለ - ጊዜያት ፡ ሊከፈል ፡ ይቻላል ። እነዚህም ፡ (፩ኛ) ከ፲፱፻፳፫ቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መታወጅ ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ ጊዜ ፡ (፪ኛ) የ፲፱፻፳፫ቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከታወጀ ፡ በኋላ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፤ እና ፡ (፫ኛ) የተሻሻለው ፡ የ፲፱፻፵፯ቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከታወጀ ፡ በኋላ ፡ ያለው ፡ ጊዜ ፡ ናቸው ። የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ለማቋቋምና ፡ ሥልጣናቸውንም ፡ ለመወሰን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የተጠቀመባቸው ፡ መብቶች ፡ በየክፍለ ፡ ጊዜው ፡ ይለያያሉ ።

#### (፩) ከ፲፱፻፳፫ቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መታወጅ ፡ በፊት ፡ ስለነበረው ፡ ክፍለ ፡ ጊዜ ፤

በዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕጋዊ ፡ እድገት ፡ ታሪክ ፡ የመጀመሪያው ፡ ክፍለ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በሦስቱ ፡ የመንግሥት ፡ ክፍሎች ፡ መካከል ፡ ማለት ፡ በሕግ ፡ አውጭው ፡ በሕግ ፡ አስፈጻሚውና ፡ በዳኝነቱ ፡ ክፍሎች ፡ የሥልጣን ፡ መከፋፈል ፡ አልነበረም ። አዲስ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ማቋቋም ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ ሕግ ፡ ማው

ጣት ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ንጉሣዊ ፡ ሕግ ፡ ያውጅ ፡ ነበረ ። ንጉሣዊ ፡ ሕግ ፡ የሚታወጅበትም ፡ የሥልጣን ፡ ምንጮች ፡ የሀገር ፡ ባሕል ፡ ልማሥና ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ነበሩ ። እንግዲህ ፡ የ፲፱፻፳፫ቱ ፡ ሕገ ፡ መንግድት ፡ ከመታወጁ ፡ በፊት ፡ በነበረው ፡ ክፍለ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ በማቋቋም ፡ ተግባር ፡ በመወሰንና ፡ ሥልጣንም ፡ በመስጠት ፡ ረገድ ፡ የነበረው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መብት ፡ ፍጹም ፡ ነበር ።

(፪) ከ፲፱፻፳፫ቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መታወጅ ፡ በኋላ ፡ ስለነበረው ፡ ክፍለ ፡ ጊዜ ፤

በሁለተኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የእድገት ፡ ታሪክ ፡ ክፍለ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በሦስቱ ፡ የመንግሥት ፡ ክፍሎች ፡ መካከል ፡ በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ የሥልጣን ፡ መከፋፈል ፡ እንዲኖር ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሲደነግጉ ፤ ፍጹም ለነበረው ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መብት ፡ በመጠኑ ፡ ገደብ ፡ ተበጀለት ። ሆኖም ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ በማቋቋምና ፡ በመቆጣጠሩ ፡ ረገድ ፡ የነበረው የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መብት ፡ እንዳለ ፡ እንዲቆይ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ። የ፲፱፻፳፫ቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፲፩ ፦

"ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ በሚሠራባቸው ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ የሥራውን ፡ አኳኋንና ፡ አቋም ፡ (አድሚኒስትራሲዮን) አጣርቶ ፡ ይወስናል" ይላል ።

ይህ ፡ አንቀጽ ፡ የሚመለከተው ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችንም ፡ ጭምር ፡ በማቋቋምና ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንባቸውንም ፡ በመወሰን ፡ ረገድ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

በ፲፱፻፳፫ቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴፬ ፡[16] እንደተመለከተው ፡ የሕዝብ ፡ መብት ፡ ነክ ፡ የሆነ ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግን ፡ የማውጣቱ ፡ ሥልጣን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ የምክር ፡ ቤቱ ፡ የጋራ ፡ ሥልጣን ፡ ነበር ። አሁን ፡ "አዋጅ" በመባል ፡ ከሚታወቀው ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰለው ፡ ይህ ፡ "ሕግ" ፡ ሊታወጅ ፡ ይችል ፡ የነበረው ፡ በሁለቱ ምክር ፡ ቤቶች ፡ ከተመከረበትና ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ ካጸደቀው ፡ በኋላ ፡ ብቻ ፡ ነበር። የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ አንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ ከአንቀጽ ፡ ፴፬ ፡ ጋር ፡ አጣምሮ ፡ በማንበብ ፡ ለነበራቸው ፡ መብት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በገዛ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ገደብ ፡ አበጅተውለት ፡ ነበር ፤ ለሚለው ፡ አስተያየት ፡ ድጋፍ ፡ ማግኘት ፡ ይቻላል ። ለራሳቸውም ፡ አስቀርተውት ፡ የነበረው ፡ ሥልጣን ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ በማቋቋም ፡ ውስጣዊ ፡ አቋማቸውን ፡ በመወሰን ፡ እና ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንባቸውን ፡ በመስጠት ፡ ረገድ ፡ ያለውን ፡ ሥልጣን ፡ ነበር ። የግለ ፡ ሰቡን ፡ መብት ፡ የሚነካ ፡ የመቆጣጠር ፡ ሥልጣንን ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚሰጥ ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግ ፡ የማውጣቱን ፡ መብት ፡ ግን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ የምክር ፡ ቤቱ ፡ የጋራ ፡ ሥልጣን፡ እንዲሆን ፡ አድርገዋል ። በ፲፱፻፳፫ቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከማንም ፡ የማይጋሩት ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሚተዳደሩበትን ፡ ውስጣዊ ፡ "ደንብ ፡" ለማውጣት ፡ የሚያስችል ፡ ሙሉ ፡ መብት ፡ ነበር ። የግለ ፡ ሰቡን ፡ መብት ፡ በቀጥታ ፡ የሚነካ ፡ ማን

---

16. የ፲፱፻፳፫ቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴፬ ፡ እንደሚከተለው ፡ ይደነግጋል ፤ "ማናቸውም ፡ ሕግ ፡ ቢሆን ፡ በምክር ፡ ቤቶች ፡ ሳይመከርበት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወዶ ፡ ሳይቀበለው ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ ሊቆም ፡ አይችልም ።"

ኛውም ፡ "ሕግ" ፡ በምክር ፡ ቤቱና ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መተባበር ፡ ባንድነት ፡ የታ ወጀ ፡ መሆን ፡ ነበረበት ። የመቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፡ ለአንድ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ መስጠት ፡ የነበረበት ፡ በ"ሕግ" ፡ መሆኑ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ[17] ፡ ከአቋቋመው ፡ አዋጅና ፡ ብረታ ፡ ብረትን ፡ ለመቆጣጠር ፡ ለተቋቋመው ፡ ቦርድ ፡ ቻርተር ፡[18] ከተሰጠበት ፡ አዋጅ ፡ ይታወቃል ።

(፫) ከተሻሻለው ፡ የ፲፱፻፵፯ቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መታወጅ ፡ በኋላ ፡ ስላ ለው ፡ ክፍለ ፡ ጊዜ ፤

የሦስቱን ፡ የመንግሥት ፡ ክፍሎች ፡ ሥልጣን ፡ የመለያየት ፡ ጥንተ ፡ ሀሳብ ፡ እና ፡ በየውስጣቸውም ፡ ያለውን ፡ ሥልጣን ፡ ሚዛን ፡ ለማስጠበቅና ፡ ለመቆጣጠር ፡ የሚያስችለው ፡ መሠረታዊ ፡ አቋም ፡ ከመጀመሪያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ይልቅ ፡ በ፲፱፻፵፯ቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ይበልጥ ፡ ተብራርቶ ፡ ይገኛል። ነገር ፡ ግን ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተው ፡ የአንቀጽ ፡ ፳፯ ቃል ፡ ከመጀመሪያው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከአንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ ቃል ፡ ጋር ፡ ሲተያይ ፡ ሰፋ ፡ ባሉ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያለው ፡ ይመስላል ። በአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ መሠረት ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ የሚሠራባቸውን ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ---"ማቋቋም ፤ ሥልጣን ፡ መስጠትና ፡ ተግባር ፡ መወሰን ፡---" ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መብት ፡ ውስጥ ፡ ነው ። በ፲፱፻፳፫ቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ መሠረት ፡ ግን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መብት ፡ የመሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ውስጣዊ ፡ አስተዳደር ፡ የሚመለከት ፡ ደንብን ፡ ማውጣት ፡ ብቻ ፡ ነበር ። እንግዲህ ፡ የአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ቃል ፡ ካንድ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውጭ ፡ ያለ ፡ ሰውን ፡ መብት ፡ የሚነካ ፡ ሥልጣንን ፡ ንጉሠ፡ ነገሥቱ ፡ ላንድ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ፤ ወደሚለው ፡ አስተሳሰብ ፡ መምራቱ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። በ፲፱፻፳፫ቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ እና ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ በአማርኛው ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሊያስተላልፍ ፡ የሚችለው ፡ ውስጣዊ ፡ አስተዳደርን ፡ የሚመለከት ፡ ደንብን ፡ ለማውጣት ፡ የሚያስችል ፡ ሥልጣንን ፡ ብቻ ፡ ነው ። አንቀጽ ፡ ፳፯ን ፡ በመመርኰዝ ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሊሰጡ ፡ ስለሚችሉት ፡ ሥልጣኖች ፡ ኋላ ፡ በምንነጋገርበት ፡ ጊዜ ፡ ቃሉ ፡ ብቻ ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ሳይ ሆን ፡ ታሪካዊ ፡ አመጣጡን ፡ በመመልከት ፡ ለአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ ጠበብ ፡ ያለ ፡ ትርጉም፡ መስጠት ፡ ተገቢ ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ እንመረምራለን ።

ለ/ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ስለተመለከቱት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መብቶች ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ ጠለቅ ፡ ብለን ፡ የምንመረምረው ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ቃል ፡ በመከተል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ በሚያቋቁምበት፣ ሥልጣን ፡ በሚሰጥበት ፡ እና ፡ ተግባር ፡ በሚወሰንበት ፡ ጊዜ ፡ ስላለው ፡ ግላዊ ፡ ወይ ም ፡ የተለየ ፡ ወይም ፡ በመልካም ፡ ፈቃዱ ፡ ላይ ፡ ስለተመሠረተው ፡ መብቱ ፡ ነው ። አሁን ፡ ባለንበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በመብታቸው ፡ የሚጠቀሙት ፡

---

17. የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፵፫ ፡ የአዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፴፩ ፡ ፲፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ።
18. የውዳቂ ፡ ብረታ ፡ ብረቶችና ፡ ብረት ፡ ያልሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ሜታሎችንም ፡ ለመቆጣጠር ፡ የተቋቋመ ፡ ቦርድ ፡ ቻርተር ፡ (በመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፷፩ ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ እንደተሻሻለው ፡) ፲፱፻፵፯፣ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፷፩ ፡ ፲፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁጥር ፡ ፬ ።

ዝቅ ፡ ብለው ፡ በተዘረዘሩት ፡ ስድስት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ነው ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የመንግሥቱ ፡ መሪ ፡ የፍትሕ ፡ ምንጭ ፡ ሕግ ፡ አውጭ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥጋዊ ፡ መሪ ፡ ጠቅላይ ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ እና ፡ ዋናው ፡ የሕግ ፡ አስፈጻሚ ፡ በመሆን ፡ በሀገሪቱ ፡ ጉዳይ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ስላላቸው ፡ ሥልጣናቸውና ፡ መብታቸውም ፡ በዚያው ፡ መጠን ፡ የተለያየ ፡ ቅጥና ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ ነው ።

በዚህም ፡ መሠረት ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ውስጥ ፡ በዝርዝር ፡ በተመለከተው ፡ መብታቸው ፡ መሠረት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ የሚከተሉትን ፡ ለማድረግ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

፩/ በአንቀጽ ፡ ፴፯ ፡ መሠረት ፡ የሕዝቡን ፡ ጥቅምና ፡ ደኅንነት ፡ ለመጠበቅ ፡ አስፈላጊና ፡ ከሌሎቹ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጋር ፡ ተስማሚ ፡ የሆኑትን ፡ እርምጃዎች ፡ ለመውሰድ ፤ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ይመስላል ።[19] ለምሳሌም ፡ ያህል የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ቻርተር ፡ በዚህ ፡ በአንቀጽ ፡ ፴፮ ፡ በተመለከተው ፡ አጠቃላይ ፡ በሆነ ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የተሰጠ ፡ ይመስላል ። የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ቻርተርም ፡[20] የተሰጠው ፡ በአንቀጽ ፡ ፴፮ ፡ በተመለከተው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

፪/ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በአንቀጽ ፡ ፴፭ ፡ እንደተመለከተው ፡ ፍትሕ ፡ በትክክል እንዲጠበቅ ፡ ማድረግ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ተግባርና ፡ መብት ፡ በመሆኑና ፡ ይህም፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣ ፡ ልማዳዊ ፡ ተግባርና ፡ መብት ፡ በመሆኑ[21] ፤ እንደዚሁም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የፍትሕ ፡ ምንጭ ፡ በመሆኑ ፡ በፍርድ ፡ የተወሰኑ ፡ ጉዳዮችን ፡ በዙፋን ፡ ችሎት ፡ ለማየት ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ፤ ስለሆነም፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፭ን ፡ በመመርኰዝ ፡ ፍትሕን ፡ በትክክል ፡ ለማስጠበቅ ፡ የሚያገለግሉ ፡ ድርጅቶችን ፡ ለማቋቋም ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፰ ፡ እና ፡ ፩፻፱ ፡ እጅግ ፡ የተወሰነ ፡ መሆኑ ፡ መዘንጋት ፡ የለበትም ።[22]

፫/ አስቀድሞ ፡ በሚሰጥም ፡ ሆነ ፡ (አንቀጽ ፡ ፻፳) ፡ በኋላ ፡ በሚሰጥ ፡ የፓርላማ ፡ ፈቃድ ፡ (አንቀጽ ፡ ፺፪) መሠረት ፡ የሕግ ፡ ማውጣትን ፡ የዳኝነትን ፡ ወይም ፡ የመቆጣጠር ፡ ሥልጣንን ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ ። ለምሳሌም ፡ ያህል ፤ ጠቅላይ ፡ ፖስታ ፡ ቤት ፡[23] አስቀድሞ ፡ በአዋጅ ፡ በተ

19. የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ቻርተር ፡ ፲፱፻፵፬ ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁ. ፩፻፹፬ ፡ ፳ኛ ፡ ዓመት ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁ. ፳ ።

20. የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በጐ ፡ አድራጐት ፡ ድርጅት ፡ የተቋቋመበት ፡ ቻርተር ፡ ፲፱፻፵፪ ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁ. ፩፻፵፫ ፡ (በመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍ. ፩፻፳፩ ፡ ፲፱፻፵፪ ፡ እንደተሻሻለው) ፡ ፲፰ኛ ፡ ዓመት ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቍ. ፲፩ ።

21. አር ፡ ኤ ፡ ሴድለር ፤ "ዘ ፡ ችሎት ፡ ጁሪስዲክሽን ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ኤምፐረር ፡ ኦፍ ፡ ኢትዮጵያ ፡- ኤ ፡ ሊጋል፡ አናሊሲስ ፡ ኢን ፡ ሂስቶሪካል ፡ ኤንድ ፡ ኮምፓራቲቭ ፡ ፐርስፔክቲቭ ፤" ጆርናል ፡ ኦፍ ፡ አፍሪካን ፡ ሎው፡ ቮሊዩም ፡ ፰ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ (፲፱፻፷፬) ፡ ገጽ ፡ ፩፻፺፯ ።

22. በሠራተኞች ፡ ጠቅላይ ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የአስተዳደር ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተቋቋመው፡ ተሻሽሎ ፡ በወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአንቀጽ ፡ ፻፱ ፡ ሳይሆን ፡ በዚሁ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአንቀጽ ፡ ፴፯ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

23. የፖስታ ፡ አገልግሎት ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፹ ፡ ፳፭ኛ ፡ ዓመት ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁጥር፡ ፳፪ ።

ሰጠ ፡ የፓርላማ ፡ ፈቃድ ፡ ደጋፊነት ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጣቸው ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ድርጅቶች ፡ ጥሩ ፡ ማስረጃ ፡ ሲሆን ፡ የሲቪል ፡ አቪዬሽን ፡ አስተዳደር ፡ ደግሞ ፡ አስ ቀድሞ ፡ ሥልጣን ፡ ከተሰጣቸው ፡ በኋላ ፡ ፓርላማን ፡ በማስፈቀድ ፡ በወጣ ፡ ረዳት ፡ ሕግ ፡ አማካይነት ፡ ይኸው ፡ ሥልጣን ፡ የጸደቀላቸው ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥ ሪያ ፡ ቤቶች ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።[24]

፬/ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፯ ፡ መሠረት ፡ በ፲፱፻፵፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕ ረቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፫፻፺፫ ፡ እና ፡ ፫፻፺፬ ፡ (የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥ ሪያ ፡ ቤቶች ፡ አቋም ፡ ለተሰጣት) ለኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የአስተዳ ደር ፡ ደንብ ፡ ሥጋዊ ፡ ውሳኔ ፡ እና ፡ ትእዛዝ ፡ ለማወጅ ፡ ይችላሉ ። ለምሳሌም ፡ የዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መታሰቢያ ፡ ቤት ፡ የቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ገዳም ፡ ቻርተር ፡[25] እና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስተዳደር ፡ ትእዛዝ ፡[26] በዚህ ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የወጡ ፡ ናቸው ።

፭/ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፱ ፡ መሠረት ፡ ለሰላም ፡ ጊዜና ፡ ለጦር ፡ ጊዜ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የጦር ፡ ኃይል ፡ ለመወሰንና ፡ ለማደርጀት ፡ ይችላሉ ። የንጉሠ ፡ ነገ ሥቱ ፡ መንግሥት ብሔራዊ ፡ ጦር ፡ የተቋቋመው ፡ በዚህ ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ነው ።[27]

፮/ በመጨረሻም ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ መሠረት ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ የሚሠራባቸውን ፡ ሚኒስቴሮችን ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍልን ፡ እና ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ለማቋቋም ፡ ሥልጣን ፡ ለመስጠትና ፡ ተግባርም ፡ ለመወሰን ፡ አስ ፈላጊው ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### ሀ/ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ስላሉት ፡ ሕገ ፡ መንግሥታውያን ፡ ገደቦች ፤

ምንም ፡ እንኳ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ውስጥ ፡ በተዘረዘረው ፡ የበላይነት ፡ ሥልጣኑና ፡ መብቱ ፡ መሠረት ፡ ትእዛዝ ፡ በማውጣት ፡ አዲስ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤትን ፡ ማቋቋም ፡ ቢችልም ፡ መሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ ዘላቂ ፡ አገልግሎት ፡ ለመስጠት ፡ የሚያስፈልገው ፡ ወጭ ፡ ከመንግሥት ፡ ገን ዘብ ፡ ሊመደብለት ፡ የሚችለው ፡ በፓርላማ ፡ በግልጽ ፡ ከተፈቀደ ፡ በኋላ ፡ መሆኑን ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፲፭ ፡ ፩፻፲፮ ፡ ፩፻፲፯ ፡ እና ፡ ፩፻፲፰ ፡ ይደነግጋሉ ። የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፲፱ም ፡ ማናቸውም ፡ የመንግሥቱ ፡ ቅርንጫፍ ፡ የሆነ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ያለፓርላማ ፡ ፈቃድ ፡ የብድር ፡ ውል ፡ መዋዋል ፡ ወይም ፡ ዋስትና ፡ መስጠት ፡ አለመቻሉን ፡ ይገልጣል ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ባወጣው ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ በሚስማማ ፡ ድንጋጌ ፡ መሠረት ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ እንደተመለከተው ፡ በሁለቱ ፡

24. የሲቪል ፡ አቪያሲዮን ፡ ድንጋጌ ፡ ፲፱፻፵፬ ፡ ድንጋጌ ፡ ቁጥር ፡ ፵፰ ፡ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ። በማጽደቂያ ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፰ ፡ ፳፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ የጸ ደቀ ።

25. ለዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መታሰቢያ ፡ ቤትና ፡ ለመንበረ ፡ ጸባኦት ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ገዳም ፡ የተሰጠ ፡ ቻርተር ፤ ፲፱፻፶ ፡ ዓ. ም. የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፱ ፡ (በመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፳፫ ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ እንደተሻሻለው ።) ፲፯ኛ ፡ ዓመት ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ።

26. የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስተዳደር ፡ ትእዛዝ ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፵፰ ፡ ፳፯ኛ ፡ ዓመት ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ።

27. የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ብሔራዊ ፡ ጦር ፡ ማቋቋሚያ ፡ ትእዛዝ ፡ ፲፱፻፶፩ ፤ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፳፩ ፡ ፲፰ኛ ፡ ዓመት ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ።

ምክር ፡ ቤቶች ፡ በተገኘ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ውሳኔ ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ሊወስድ ብት ፡ ይችላል ። እንግዲህ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ሦስቱን ፡ የመንግ ሥት ፡ ክፍሎች ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ የመቆጣጠርና ፡ የሥልጣን ፡ ተመጣጣኝነትንም ፡ የማ ስጠበቅ ፡ ባሕረ ፡ አሳብ ፡ (ዶክትሪን) በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ ወሰን ፡ አበጅቶበታል ፡ ማለት ፡ ነው ።[28] ዘ ፡ ሎው ፡ ሜኪንግ ፡ ፕሮሴስ ፡ ኢን ፡ ኢትዮፒያ ፡ (በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ አወጣጥ ፡ ሥርዓት) የሚለውን ፡ ድርሰት ፡ በመመልከት ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ስለሚገኘው ፡ የሦስቱ ፡ የመንግሥት ፡ ክፍሎች ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ የመ ቆጣጠርና ፡ የሥልጣን ፡ ተመጣጣኝነትን ፡ የማስጠበቅ ፡ ዶክትሪን ፡ እና ፡ የመንግሥ ቱም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ ስላላቸው ፡ የመቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፡ ይረዷል ።

እንግዲህ ፡ ለአንድ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ መሠረት ፡ በወጣ ፡ ትእዛዝ ፡[29] አማካይነት ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችል ፡ ሥልጣን ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በተለይም ፡ በአንቀጽ ፡ ፹፰ ፡ ፺፪ ፡ ፩፻፲፩-፩፻፲፱ ፡ እና ፡ በ፩፻፳፪ ፡ ውሱን ፡ ነው ።

## ለ/ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ ከሌሎች ፡ አንቀጾች ፡ ጋር ፡ ሲነፃፀር ።

በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መብት ፡ ላይ ፡ ወሰን ፡ የሚያበጅ ፡ ማንኛውም ፡ የሕግ ፡ ቃል ቢሆን ፡ ከተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩ ፡ ጋር ፡ ሲተያይ ፡ ሊጸና ፡ የማይ ችል ፡ መስሎ ፡ ይታያል ። ይህም ፡ የተባለበት "---ሥልጣኑ ፡ የማይደፈር ---" የሚል፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ በአንቀጽ ፡ ፩ ፡ ውስጥ ፡ ስለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ ተጠቅሶ ፡ ስለ ሚገኝ ፡ ነው ።

ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ የመንግሥቱን ፡ ግዛት ፡ መከላ ከያና ፡ አንድነት ፡ የነዋሪዎቹንም ፡ ጥቅምና ፡ ደህንነት ፡ በመጠበቅ ፡ ረገድ ፡ ያለበት ፡ ተግባር ፡ (አንቀጽ ፡ ፴፮)፤ ወይም ፡ የበላይ ፡ ገዥ ፡ በመሆን፡ በአገሩ ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ ላይ፡ በከፍተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ለመጠቀም ፡ ያለው ፡ መብት ፡ (አንቀጽ ፡ ፳፮) ፤ ወይም ፡ ከው ጭ ፡ አገር ፡ ጋር ፡ የሚደረገውን ፡ ግንኙነት ፡ የበላይ ፡ ሆኖ ፡ የመምራት ፡ ሥልጣን ፡ (አንቀጽ ፡ ፴) ፤ እነዚህ ፡ የተዘረዘሩት ፡ በሙሉ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ቃል ፡ በመተ ላለፍ ፡ ሊፈጸሙ ፡ የማይችሉ ፡ ናቸው ። ይህንኑ ፡ ለማሳወቅ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መን ግሥት ፡ ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መብትና ፡ ሥልጣን ፡ ሲዘረዝር ፡ "---በዚ ህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እንደተወሰነው---" (አንቀጽ ፡ ፳፮) ፤ እና ፡ "--- በዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተጻፉት ፡ ቃሎች ፡ ሳይጓደሉ ፡ ---" (አንቀጽ ፡ ፴፮) የሚሉትን ፡ መወሰ ኛ ፡ ቃሎች ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ። እነዚህ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መብትና ፡ ሥልጣን ፡ የሚዘረዝ ሩት ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ መግቢያና ፡ መደምደሚያ ፡ አን ቀጾች ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መብትና ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ የተጣሉትንም ፡ ገደቦች ፡ በዝርዝር ፡ ጠቅሰው ፡ ይገኛሉ ።

---

28. ኬኔት ፡ ሬድን ፡ ዘ ፡ ሎ ፡ ሜኪንግ ፡ ፕሮሴስ ፡ ኢን ፡ ኢትዮፒያ ፡ (፲፱፻፷፯) አዲስ ፡ አበባ ፡ ገጽ ፡ ፯-፰።

29. አንድ ፡ ትእዛዝ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግ ፡ ማለትም ፡ ከፍተኛ ፡ የሕግ ፡ አስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ሕግ ፡ ፎርም ፡ ቢሆንም ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአንቀጽ ፡ ፹፰ ፡ ፹፱ ፡ ወይም ፡ ፺ ፡ መሠረት ፡ ከወጣ ፡ አዋጅ ፡ ወይም ፡ በዚሁ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ መሠረት ፡ ከወጣ ፡ ድን ጋጌ ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ነው ። በነገራችን ፡ ላይ ፡ የበላይ ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌ ፡ በሆነው ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ "ትእዛዝ ፡" የሚባለውን ፡ የሕግ ፡ ፎርም ፡ አይጨምርም ፤ (ይህም ፡ ከተሳሳተ ፡ አተረጓጎም ፡ የተነሳ ፡ ነው ።) ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፹፰ ፡ "ትእዛዝን" ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ መታተም ፡ ይገባቸዋል ፡ ሲል ፡ ከሚዘረዝራቸው ፡ ሕጎች ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ አድርጎ ፡ ይጠቅሰዋል ።

እንግዲህ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሥልጣኖች ፡ በሙሉ ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አንቀጾች ፡ ገደብ ፡ የተደረገላቸው ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ። ይህም ፡ ከሆነ ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በአንቀጽ ፡ ፷፮ም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሌሎች ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጾች ፡ መሠረት ፡ ሊሰጡ ፡ የሚችሉት ፡ ሥልጣኖች ፡ የንጉሠ፡ ነገሥቱን ፡ ሥልጣኖች ፡ የሚወስኑትን ፡ ሌሎች ፡ የሕገ፡ መንግሥቱን፡ አንቀጾች፡ ሊተላለፉ ፡ አይችሉም ። ወደፊት ፡ የሚሠሩ ፡ ሕጎች ፡ ከዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት፡ እና፡ ኢትዮጵያ ፡ ተካፋይ ፡ ከምትሆንባቸው ፡ ከኢንተርናሽናል ፡ ውሎች ፡ ስምምነቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ ሲሆኑ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ ፡ ብሎ ፡ በሚወስነው ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተው ፡ የበላይ ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች፡ የሚሰጣቸው ፡ ሥልጣኖች ፡ አንቀጽ ፡ ፬ ፡ ስላለ ፡ በሕጋዊነታቸው ፡ ረገድ ፡ ሊመረመሩ ፡ የማይችሉ ፡ ናቸው ፡ የሚለውን ፡ ክርክር ፡ ውድቅ ፡ ያደርገዋል ። ይህም ፡ የሚሆንበት ፡ ምክንያት ፡ ከሌሎቹ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጾች ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ የሥልጣን ፡ መተላለፍ ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ የማያገለግል ፡ ይሆናል ፡ ወደሚለው ፡ አስተያየት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፪ ፡ በግድ ፡ ስለሚመራ ፡ ነው ።

ይህ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አንቀጾች ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ መሠረታዊ ፡ አለመስማማት ፡ በሆነው ፡ መንገድ ፡ መወገድ ፡ አለበት ። ደራሲው ፡ ይህን ፡ ለማድረግ ፡ የሚሞክረው ፡ "አለመስማማት ፡ ካለ ፡ ስለጠቅላላ ፡ ጉዳይ ፡ ከሚወስነው ፡ ሕግ ፡ ይልቅ ፡ ስለአንድ ፡ ጉዳይ ፡ በተለይ ፡ የሚደነግገው ፡ ሕግ ፡ የጸና ፡ ይሆናል ፡" በሚለው ፡ ሲያያዝ ፡ በመጣው ፡ በሕግ ፡ አተረጓጎም ፡ ዘዴ ፡ ነው ። አንቀጽ ፡ ፬ ፡ ስለ ጠቅላላ ፡ ጉዳይ ፡ ከሚወስነው ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ክፍል ፡ ስለሚገኝ ፡ ስለአንዳንድ ፡ ጉዳይ ፡ በተለይ ፡ የሚወስኑት ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጾች ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ የበላይነት ፡ ሊኖራቸው ፡ ይገባል ። እንዲህም ፡ ማለት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መብት ፡ ላይ፡ ገደብ ፡ የሚያበጁት ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፷፮ ፡ ፴፮ ፡ ፹፰-፺፪ ፡ ፩፻፳፪ ፡ እና፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ ገደብ ፡ ለማበጀትም ፡ ሆነ ፡ ሚዛን ፡ ለመፍጠር ፡ የታቀዱት ፡ ሌሎቹ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጾች ፡ የአንቀጽ ፡ ፬ን ፡ ቃል ፡ እንደሚወስኑት ፡ ተደርጎ ፡ መታሰብ ፡ አለበት ።

ቀደም ፡ ሲል ፡ የተዘረዘሩት ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ በየቦታው ፡ የሚገኙት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መብቶችና ፡ ሥልጣኖች ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉዳዮች ፡ የሚያገለግሉ ፡ ናቸው ። ለዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ግን ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፷፮ ፡ የተመለከተው ፡ ቢሆንም ፡ ለዚሁ ፡ የሚደረገው ፡ ጥልቅ ፡ ምርምር ፡ ለሌሎቹ ፡ ምርምር ፡ መመሪያ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የአንቀጽ ፡ ፷፮ ፡ ጥልቅ ፡ ምርምር ።

የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፷፮ ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ እንደሚከተለው ፡ ይነበባል ።

"ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚኒስቴሮችን ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ የሚሠራባቸውን ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችና ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ አቋም ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር ፡ ሁሉ ፡ ይወስናል ፤ የነዚህንም ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ይሾማል ፤ በማዕረግ ፡ ያሳድጋል ፤ ያዛውራል ፤ ከሥራ ፡ ያግዳል ፤ ይሽራልም ።"

እዚህ ፡ ላይ ፡ የአማርኛው ፡ ቃል ፡ ከእንግሊዝኛው ፡ የአንቀጽ ፡ ፹፯ ፡ ቃል ፡ እንደሚለይ ፡ ይገነዘቧል ። የአማርኛው ፡ ቃል ፡ እንደሚከተለው ፡ ይነበባል ።

"ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ የሚሠራባቸውን ፡ የመሥሪያ ፡ ቤቶችንና ፡ የሚኒስቴሮችን ፡ ሁሉ ፡ የሥራ ፡ አኳኋን ፡ አቋቁሞ ፡ ይወስናል ። የመሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ባለሥልጣን ፡ ይሾማል ፤ በማዕረግ ፡ ያሳድጋል ፤ ያዛውራል ፤ ከሥራ ፡ ያግዳል፤ ይሽራልም ።"

በእንግሊዝኛውና ፡ በአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ መካከል ፡ ከሚታየው ፡ የዓረፍተ ፡ ነገር ፡ ልዩነት ፡ ማለት ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ አንድ ፡ ረጅም ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር፡ ሲሆን ፡ የአማርኛው ፡ ደግሞ ፡ ሁለት ፡ አጫጭር ፡ ዓረፍተ ፡ ነገሮች ፡ ከመሆኑ ፡ ሌላ ፡ ሁለቱ ፡ ጽሑፎች ፡ ሲወዳደሩ ፡ የሚከተሉት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ የፍሬ ፡ ነገር ፡ ልዩነቶች ፡ ይገኙባቸዋል ። አንደኛ ፤ በአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ሚኒስቴሮችና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ብቻ ፡ ሲጠቀሱ ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ ሚኒስቴሮች ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችና ፡ የመንግሥቱ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራባቸው ፡ ክፍሎች ፡ ሁሉ ፡ ተዘርዝረው ፡ ይገኛሉ ። ሁለተኛ ፤ "--- የሥራ ፡ አኳኋን ፡ አቋቁሞ፡ይወስናል ። ---" የሚል ፡ ትርጉሙ ፡ ግልጽ ፡ ያልሆነ ፡ ሐረግ ፡ በአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ሲገኝ፣ " --- አቋም ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባር--" የሚሉት ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ። ሦስተኛ ፤ የአማርኛው ፡ ቃል ፡ በመጀመሪያው ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ሚኒስቴሮችንና ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ የሚሠራባቸውን ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሲጠቅስ ፡ በሁለተኛው ፡ ዓረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ግን፡ የሚጠቅሰው ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ብቻ ፡ ነው ። "የነዚህንም ፡" የሚለው ፡ በአንቀጹ ፡ በስተመጨረሻ ፡ የሚገኘው ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ቃል ፡ እንደሚያመለክተው ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ አንቀጹ ፡ የሚናገረው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ስለሚያቋቁማቸው ፡ ስለሦስቱም ፡ ዓይነት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ይመስላል ።

ባጭሩ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፹፯ ፡ የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ የ፲፱፻፹፫ቱን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የአንቀጽ ፡ ፲፮ን ፡ ማለትም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚኒስቴሮችን ፡ እና ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍሎችን ፡ ማቋቋምና ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንባቸውንም ፡ ለመወሰን ፡ ብቻ ፡ ሲችል ፡ ሥልጣን ፡ የመስጠቱን ፡ መብት ፡ ግን ፡ ከፓርላማ ፡ ጋር ፡ ይጋራዋል ፡ የሚለውን ፡ መንፈስ ፡ ያዘለ ፡ ይመስላል ። የእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ግን ፡ ሚኒስቴሮችን ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ እና ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ የሚሠራባቸውን ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ የማቋቋም ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አንዳንድ ፡ ወሰኖችን ፡ ሳይተላለፍ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ሕግ ፡ በማውጣት ፡ ሥልጣን ፡ የመስጠትና፡ ተግባር ፡ የመወሰንን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መብት ፡ እንደያዘ ፡ አድርጎ ፡ ሊነበብ ፡ ይችላል ።

በእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኘው ፡ "ተግባር" ፡ በሚለው ፡ ፋንታ ፡ "የሥራ ፡ አኳኋን ፡ አቋቁሞ ፡ መወሰን ፡" የሚለውን ፡ ትርጉሙ ፡ ግልጽ ፡ ያልሆነውን ፡ በአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ሐረግ ፡ መተካት ፡ ቢቻልም ፡ "ሥልጣን" ለሚለው ፡ ለእንግሊዝኛው ፡ ቃል ፡ በአማርኛው ፡ የአንቀጽ ፡ ፹፯ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ተመሳሳይ ፡ አይገኝለትም ። "ሥልጣን" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በዚህ ፡ ጽሑፎችን ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ያለው ፡ ስለሆነ ፡ ሁለት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ጥያቄዎችን ፡ ጠልቆ ፡ መመርመር ፡ ይገባናል ። አንደኛ ፤ "ሥልጣን" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በአማርኛው ፡ ውስጥ ፡ አለመጨመሩ ፡ ታስቦ ፡ የተደረገ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ባለማወቅ ፡ (በዝንጋታ)? ሁለተኛ ፤ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአንቀጽ ፡ ፹፯ ፡ በእንግሊዝኛውም ፡ ሆነ ፡ በአማርኛው ፡ ውስጥ ፡ "ሥልጣን" የሚለውን ፡ ቃል ፡ እንዳለ ፡ አድርገን ፡ ግን

በብ ፡ ይገባናል ፡ ብለን ፡ ብንወስን ፡ አንቀጹ ፡ ሲወጣ ፡ በሕግ ፡ አውጭው ፡ ክፍል ፡ ሀሳብ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩት ፡ ሊሰጡ ፡ የሚችሉት ፡ ሥልጣኖች ፡ ምን ፡ ምን ፡ ናቸው ?

በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ አስተያየት ፡ በአማርኛውና ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ቃል ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ መኖሩ ፡ ሕግ ፡ አውጭው ፡ አስቦ ፡ ያደረገው ፡ ሳይሆን ፡ ከትርጉም ፡ ጉድለት ፡ የተነሣ ፡ ነው ። "ሥልጣን" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ "ተግባር ፡" ከሚለው ፡ ጋር ፡ ተዛማጅ ፡ አብሮ ፡ ሂያጅ ፡ ስለሆነ ፡ ሁለቱንም ፡ ቃላት ፡ ይዞ ፡ የሚገኘውን ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ ከተመለከተው ፡ "አቋም ፡" ከሚለው ፡ ቃል ፡ ጋር ፡ የሚያስተሳስራቸው ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ቃል ፡ ከአማርኛው ፡ ይልቅ ፡ በትክክለኛ ፡ አስተሳሰብ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ይመስላል ።

የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ የተተረጐመው ፡ በመጀመሪያ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ከተረቀቀ ፡ በኋላ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ በአማርኛውና ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ቃል ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ የተገኘበት ፡ ምክንያት ፤ ረቂቁ ፡ በትክክል ፡ ባለመተርጐሙ ፡ እንጂ ፡ ሕግ ፡ አውጭው ፡ ክፍል ፡ ፈቅዶ ፡ ያደረገው ፡ አይመስልም ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ ሕግ ፡ አውጪዎቹ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ይልቁንም ፡ የፓርላማው ፡ አባሎች ፡ ተመልክተው ፡ የመከሩበት ፡ የአማርኛውን ፡ ጽሑፍ ፡ ስለሆነ ፡ ይኸው ፡ እንደሕግ ፡ አውጭዎቹ ፡ እርግጠኛ ፡ ፍላጎት ፡ ሊቆጠርና ፡ ለእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ የበላይ ፡ በመሆን ፡ የጸና ፡ እንደሆነ ፡ ተደርጎ ፡ መገመት ፡ አለበት ፤ የሚል ፡ ክርክር ፡ ማቅረብ ፡ ይቻላል ። ይህንንም ፡ ክርክር ፡ ለማጠንከር ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ መደበኛ ፡ (ኦፊሲየል) ቋንቋ ፡ አማርኛ ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፳፭ ፡ መጥቀስ ፡ ይቻላል ።

ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ የአማርኛውንና ፡ የእንግሊዝኛውን ፡ ጽሑፍ ፡ እንደምን ፡ ማስማማት ፡ ይቻላል ?

የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ግልጽ ፡ ባለመሆኑ ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉሙን ፡ ለማወቅ ፡ መተርጐምን ፡ ይጠይቃል ። ትክክለኛ ፡ ትርጉሙን ፡ ለማወቅ ፡ ከሚረዱት ፡ ዘዴዎች ፡ አንዱ ፡ የሁለቱን ፡ ማለት ፡ የእንግሊዝኛውንና ፡ የአማርኛውን ፡ ጽሑፍ ፡ ማወዳደርና ፡ ወደዋንቱ ፡ ረቂቅም ፡ መመለሱ ፡ ነው ። የሁለቱን ፡ ቃል ፡ በማወዳደር ፡ የሚገኘውን ፡ ከላይ ፡ ዘርዝረን ፡ የጠቀስነውን ፡ ልዩነት ፡ እና ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ መጀመሪያ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ መረቀቁን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የቀረው ፡ ቢቀር ፡ የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ጉድለት ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ሊሟላ ፡ ይገባል ፤ ለሚለው ፡ ክርክር ፡ አንድ ፡ ድጋፍ ፡ እናገኛለን ።

የእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ በጠባቡ ፡ መተርጐም ፡ አለበት ፡ ለሚለው ፡ ክርክር፡ የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ትርጉሙ ፡ የሚፈለገውን ፡ ያህል ፡ ግልጽ ፡ ባይሆንም ፡ አንድ፡ ድጋፍ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ይህም ፡ የተባለበት ፡ ምክንያት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ሊሰጥ ፡ የሚቻለው ፡ ሥልጣን ፡ የመንግሥቱንና ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ውስጣዊ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ለመቆጣጠር ፡ የሚያስችል ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ የሚያመለክት ፡ ትርጉም ፡ አንቀጹ ፡ ይዞ ፡ የሚገኝ፡ ስለሚመስል ፡ ነው ። በሌላ ፡ አነጋገር ፡ እንደአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ን ፡ በመመርኰዝ ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሊሰጡ ፡ የሚችሉት ፡ ሥልጣኖች ፡ በዓላማም ፡ ሆነ ፡ በአፈጻጸም ፡ ገደብ ፡ የተበጀላቸው ፡ናቸው።

ለ/ <u>በአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ ስር ፡ ሊሰጡ ፡ ስለሚችሉት ፡ ሥልጣኖች ፡ ዓይነት</u> ።

በአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ በዓላማም ፡ ሆነ ፡ በአፈጻጸም ፡ የተወሰነና ፡ ገደብም ፡ የተበጀለት ፡ ስለሆነ ፡ ቃሉን ፡ በመመርኰዝ ፡ ሕጋዊ ፡

ተፈጻሚነት ፡ ያለው ፡ የመቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ መስጠት ፡ አይቻልም ። "ሥልጣን" ፡ የሚለውን ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ውስጥ፡ በግልጽ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ቃል ፡ የአማርኛውን ፡ የአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ ጽሑፍ ፡ መመሪያ ፡ በማድረግ ፡ በጠባቡ ፡ መተርጐምና ፡ በሌሎች ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ማለት ፡ በተራ ፡ ዜጎች ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ለመስጠት ፡ የሚያስችል ፡ ሳይሆን ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ በሚሠራባቸው ፡ እና ፡ በአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ውስጣዊ ፡ አስተዳደር ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ለመስጠት ፡ እንደሚያስችል ፡ ተደርጐ ፡ መገመት ፡ አለበት ። ባጭሩ፡ የአንቀጽ ፡ ፳፯ን ፡ የአማርኛውንና ፡ የእንግሊዝኛውን ፡ ጽሑፍ ፡ ከመረመሩና ፡ ካነፃጸሩ ፡ በኋላ ፡ እንደሚከተለው ፡ ለመወሰን ፡ ይቻላል ።

(፩) የእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ከአማርኛው ፡ ይልቅ ፡ በትክክለኛ ፡ አስተሳሰብ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ስለሆነ ፡ የአማርኛውን ፡ ጽሑፍ ፡ ትርጉም ፡ በሚገባ ፡ ለማወቅ ፡ እንደማብራሪያ ፡ ሊጠቀሙበት ፡ ይቻላል ።

(፪) የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ አተረጓጐም ፡ የእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ በግልጽ ፡ እንደሚለው ፡ ሊነበብ ፡ ይገባል ፤ ምክንያቱም ፡ የሚኒስቴሮችን ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍልና ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ የሚሠራባቸውን ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የማቋቋም ፡ መብት ፡ የቀረው ፡ ቢቀር ፡ ለነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ አንዳንድ ፡ ሥልጣኖችን ፡ የመስጠትንም ፡ መብት ፡ እንደሚይዝ ፡ መገመት ፡ ይገባዋል ። አሁን ፡ እንዳለው ፡ የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ የሆነ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያለው ፡ አንዳችም ፡ ሥልጣን ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፯፡ መሠረት ፡ መስጠት ፡ አይቻልም ።

እንግዲህ ፡ የሚቀጥለው ፡ ጥያቄ ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ሕግን ፡ በማውጣት ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ሥር ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችላቸው ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያላቸው ፡ ሥልጣኖች ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ናቸው ? የሚለው ፡ ነው ። እንደደራሲው ፡ አተረጓጐም ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ መሠረት ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችለው ፡ ሥልጣን ፡ ዓይነት ፤ (፩) የመቆጣጠርን ፡ ሥልጣን ፤ ለምሳሌ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ውስጣዊ ፡ አስተዳደር ፡ ሳይሆን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖችን ፡ ማለት ፡ ተራ ፡ ዜጎችን ፡ የመቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፤ (፪) የፖሊስን ፡ ሥልጣን ፡ የሚመስል ፡ ሥልጣን ፤ ለምሳሌ ፡ አዲስ ፡ ወንጀሎችን ፡ በሕግ ፡ የመወሰን ፤ ወይም ፡ አስቀድሞ ፡ በወጡ ፡ ቅጣቶች ፡ ምትክ ፡ አዳዲስ ፡ ቅጣቶችን ፡ የማወጅ ፤ ወይም ፡ ደንቦችን ፡ በፍርድ ፡ የማስፈጸም ፡ ሥልጣን ፤ (፫) በግልጽም ፡ ሆነ ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ ለፓርላማ ፡ የተሰጠ ፡ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ነክ ፡ ጉዳዮችን ፡ የመቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፡ የሚጨምር ፡ መሆን ፡ የለበትም ።

ከላይ ፡ በዝርዝር ፡ ከጠቀስናቸው ፡ በስተቀር ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ መሠረት ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሊሰጡ ፡ የሚችሉት ፡ ሥልጣኖች ፡ የአስፈጻሚውን ፡ የሕግ ፡ አውጭውንና ፡ የዳኝነቱን ፡ ክፍል ፡ ሥልጣኖች ፡ የሚመስሉ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ ። ባጭሩ ፡ የመቆጣጠር ፡ ያልሆኑ ፡ ሥልጣኖች ፡ የአንድን ፡ ዜጋ ፡ ሕይወት ፡ ነፃነት ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ያለሕጋዊ ፡ አፈጻጸም ፡ የማያሳጡ ፡ ሥልጣኖች ፡ ታክስ ፡ ወይም፡ ግብር ፡ ለመጣል ፡ የማያስችሉ ፡ ሥልጣኖች ፡ የመንግሥትን ፡ ገንዘብ፡ ወጭ፡ ለማድረግ ፡ የማያስችሉ ፡ ሥልጣኖች ፡ እና ፡ ያለፓርላማ ፡ ፈቃድ ፡ ገንዘብ ፡ ለመበደር ፡ የማያስችሉ ፡ ሥልጣኖች ፡ ሁሉ ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ መሠረት ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሊሰጡ ፡ የሚችሉ ፡ ሥልጣኖች ፡ ናቸው ። ሊሰጡ ፡ የማይቻሉ ፡ ስንል ፡ የዘረዘርናቸውን ፡ መሠረታውያን ፡ ሥልጣኖች ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በሚገባ ፡ ለመስጠት ፡ የተፈለገ ፡ እንደሆነ ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ በሕግ ፡ በተ

ለይም ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ የተደነገገው ፡ አፈጻጸም ፡ (ፎርም) መጠበቅ ፡ አለበት ፤ ማለታችን ፡ ነው ።

አንዳንድ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ለማቋቋም ፡ ዘወትር ፡ በዝግታ ፡ የሚንቀሳቀሰውን ፡ የሕግ ፡ አውጭውን ፡ ክፍል ፡ ሳይጠብቅ ፡ አንዳንድ ፡ ተፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ መሠረታውያን ፡ ሥልጣኖችን ፡ ለመስጠት ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ ሊመኝ ፡ ስለሚችል ፡ ይህ ከላይ ፡ የተሠነዘረው ፡ አስተያየት ፡ ችግር ፡ መፍጠሩ ፡ አይቀርም ። የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ አንድን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ማቋቋምና ፡ ሥልጣኑንም ፡ የሕግ ፡ አውጭው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ ከመከሩበት ፡ በኋላ ፡ ሳይሆን ፡ ወዲያው ፡ በትእዛዝ ፡ ወይም ፡ በቻርተር ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ይታየው ፡ ይሆናል ። እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ አንድን ፡ እቅድ ፡ አሟልቶ ፡ ማቅረብ ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ ሊገኝበት ፡ ይችላል ። በእነዚህ ወይም ፡ በሌሎች ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ከነዚህ ፡ ባንዱ ፡ የተነሣ ። በአዋጅ ፡ ወይም ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ቃል ፡ ተሟልቶ ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ በድንጋጌ ፡ መውጣት ፡ የሚገባውን ፡ ሕግ ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ን ፡ በመመርኰዝ ፡ በትእዛዝ ፡ ሲያወጣ ፡ ይታያል ።

የዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ቻርተር ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ? እንዲህ ፡ ያለው ፡ ቻርተር ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ታትሞ ፡ በሚወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ መደረግ ፡ ይገባዋል ? በዚህ ፡ ረገድ ፡ ለሚነሳው ፡ ችግር ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆን ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ እንደምሳሌ ፡ መውሰድ ፡ ይቻላል ። የደራሲውን ፡ አስተያየት ፡ እንደሚከተለው ፡ ባጭሩ ፡ መግለጥ ፡ ይቻላል ። አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የታየን ፡ የአንድ ፡ አዲስ ፡ የተቋቋመን ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አቋም ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ መሠረት ፡ በወጣ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመወሰን ፡ በቂ ፡ ምክንያቶች ፡ ቢኖሩም ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ “የሕግ ፡ ማውጣት” ፡ ሥልጣን ፡ ውጭ ፡ የታወጁትን ፡ ሕጎች ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ሥር ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዳላቸው ፡ ለማድረግ ፡ በቂ ፡ ምክንያቶች ፡ አይሆኑም ። የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ የሚያደርገው ፡ ሁሉ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በዝርዝር ፡ ከተወሰኑት ፡ ሥልጣኖቹ ፡ ውጭ ፡ መሆን ፡ እንደማይገባው ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ሊገምት ፡ ይገባዋል ። ስለዚህ ፡ በደራሲው ፡ አስተያየት ፡ ከሥልጣን ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ያወጣቸው ፡ የሕግ ፡ ቃሎች ፡ በትእዛዝ ፡ ወይም ፡ በቻርተር ፡ ውስጥ ፡ ተመልክተው ፡ ቢገኙ ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት፡ እንዲኖራቸው ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ ክፍል ፡ ተጨማሪ ፡ ሕግ ፡ ማውጣት ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ ተደርገው ፡ መተርጐም ፡ ይገባቸዋል ። የተባሉት ፡ ቃሎች ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ የሚኖራቸው ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ተጨማሪ ፡ ድርጊት ፡ (እርምጃ) ሲወሰድ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ሥልጣን ፡ በመወሰን ፡ ረገድ ፡ ስላለው ፡ መብት ፤

### የመደምደሚያ ፡ አስተያየት ።

ከላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፡ እንደዚሁም ፡ የተደረገውም ፡ ጥልቅ ፡ ምርምር ፡ ጭምር ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ ጠበብ ፡ ያለ ፡ ትርጉም ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባል ፡ ወደሚለው ፡ አስተያየት ፡ ይመራሉ ። ሌሎች ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጾች ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ ከጣሉዋቸው ፡ ገደቦች ፡ የተነሣ ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ የተመለከተው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ አንድን ፡ የአስ

ተዳደር ፡ ክፍል ፡ *መሥሪያ* ፡ ቤትን ፡ ለማቋቋም ፡ ውስጣዊ ፡ *ሥልጣኑንና* ፡ ተግባሩን ፡ አቋሙንም ፡ ጭምር ፡ ለመወሰን ፡ ብቻ ፡ የሚያስችል ፡ ነው ። በሌላ ፡ አነጋገር ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ መሠረት ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ *መሥሪያ* ፡ ቤት ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችለው ፡ *ሥልጣን* ፡ *የመሥሪያ* ፡ ቤቱን ፡ አቋም ፡ ውስጣዊ ፡ ጉዳይና ፡ ተግባርን ፡ የሚመለከት ፡ መሆን ፡ ሲገባው ፡ የመቆጣጠርን ፡ የፖሊስ ፡ መሰልን ፡ እና ፡ በግልጽም ፡ ሆነ ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ ለፓርላማ ፡ የተሰጠን ፡ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ነክ ፡ ጉዳይ ፡ የመቆጣጠር ፡ ሥልጣንን ፡ ሊጨምር ፡ አይችልም ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

### በአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ በወጣ ፡ ሕግ ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ *መሥሪያ* ፡ ቤቶች ሊሰጡ ፡ ስለሚችሉት ፡ ሥልጣኖች ፡ ዓይነት ፤

በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፮ ፡ የተጣለበትን ፡ ኃላፊነትና ፡ ተግባር ፡ ለማሟላትና ፡ ለመፈጸም ፡ ሙሉ ፡ ገዥና ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ የበላይ ፡ በመሆኑ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የማይከለክለውን ፡ ለሕዝቡ ፡ ጥቅምና ፡ ደህንነት ፡ የሚበጀውን ፡ ማንኛውንም ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ተግባሩን ፡ የሚፈጽምበት ፡ አንዱ ፡ መንገድ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ መሠረት ፡ በማቋቋም ፡ ተግባራቸውን ፡ በመወሰንና ፡ ሥልጣንም ፡ በመስጠት ፡ ነው ።

በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ሕጎች ፡ የሚወጡት ፡ "ትእዛዝ ፡" "የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ " እና ፡ "የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡" በሚል ፡ ስያሜ ፡ በሚጠሩ ፡ የሕግ ፡ ዓይነቶች ፡ (ፎርም) ፡ ነው ። መሠረታውያን ፡ ሕጎች ፡ ግን ፡ የሚወጡት ፡ በ"አዋጅ" ፡ ወይም ፡ በ"ድንጋጌ" ፡ መልክ ፡ ነው ።

ሚስተር ፡ ክራውን ፡ በጽሑፋቸው ፡ እንደገለጡት ፡ ሁሉ ፡ "የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ የሚያወጣቸው ፡ ሕጎች ፡ ዓይነታቸው ፡ ሁለት ፡ ነው ። ከነዚህም ፡ አንደኛው ፡ ዓይነት ፡ በመሠረቱ ፡ ስለአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ ውስጣዊ ፡ አቋም ፡ የወጣ ፡ በመሆኑ ፡ የአስተዳደሩን ፡ ክፍል ፡ የአሁንና ፡ የወደፊት ፡ አባሎች ፡ ብቻ ፡ የሚመለከት ፡ ሕግ ፡ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ፡ ዓይነት ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ ሕብረተ ፡ ሰቡን ፡ የሚመለከት ፡ ሌሎችን ፡ ሕጎች ፡ ለማሟላት ፡ የሚወጣ ፡ ሕግ ፡"[30] ነው ።

የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ስላወጣቸው ፡ ሕጎች ፡ የሚደረግ ፡ ጠቅላላ ፡ ምርምር ፡ እንደሚያመለክተው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ባለሥልጣኖች ፡ *የመሥሪያ* ፡ ቤታቸውን ፡ ውስጣዊ ፡ አቋምና ፡ ባንዳንድ ፡ በተወሰኑ ፡ *መሥሪያ* ፡ ቤታቸውን ፡ በሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ደንብ ፡ የማውጣት ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቷቸው ፡ ይገኛል ።

ነገር ፡ ግን ፡ በሁለተኛው ፡ ማለት ፡ የሕዝቡን ፡ መብት ፡ የሚነኩ ፡ ሕጎችን ፡ በማውጣት ፡ ወይም ፡ በጠቅላላው ፡ ኅብረተ ፡ ሰብ ፡ ላይ ፡ አዳዲስ ፡ ግዴታዎችን ፡ በመጣል ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ገደብ ፡ ሊኖር ፡ ይገባል ። ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ *መሥሪያ* ፡ ቤት ፡ በአዋጅ ፡ ወይም ፡ በድንጋጌ ፡ ውስጥ ፡ በግልጽ ፡ የተመለከተ ፡ *መመሪያ* ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር ፡ በአንድ ፡ ሙያ ፡ ላይ ፡ የተሰ

---

30. ኢ ፡ ኤስ ፡ ኮርዊን ፡ ዘ ፡ ፕሬዚደንት ፡ (ኦፊስ ፡ ኤንድ ፡ ፓወርስ ፡ ፩ሺ፯፻፹፯-፩ሺ፱፻፶፯) (፬ኛ ኤዲሺን ፩ሺ፱፻፶፯) ፡ ኒውዮርክ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ፕሬስ ፡ ኒውዮርክ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፺፫ ።

ማሩ ፡ ሰዎችን ፡ ቁጥር ፡ ወይም ፡ የሥራ ፡ ሁኔታ ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ባወጣው ፡ ሕግ ፡ ብቻ ፡ እንዲቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፡ ሊሰጠው ፡ አይገባም ። ምክንያቱም ፡ የሥልጣን ፡ መቆጣጠር ፡ ጥንተ ፡ ሀሳብ ፡ የሌለበት ፡ ሥልጣን ፡ በራስ ፡ አስተያየት ፡ ብቻ ፡ መመራትንና ፡ ሕግ ፡ መጣስንም ፡ ሊያስከትል ፡ ስለሚችል ፡ ነው ።

አንድ ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የተሰጠ ፡ በአዋጅ ፡ ወይም ፡ በድንጋጌ ፡ መልክ ፡ በወጣ ፡ ሕግ ፡ ያልተደገፈ ፡ ሥልጣን ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ይኖረው ፡ ወይም ፡ አይኖረው ፡ እንደሆነ ፡ ለማሳየት ፡ በአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ አማካይነት ፡ ስለተሰጡት ፡ ሥልጣኖች ፡ ቀጥለን ፡ የተለየ ፡ ጥናት ፡ እናደርጋለን ። አስቀድመን ፡ የአዋሽን ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ ሕጋዊ ፡ መልክ ፡ (ፎርም) ፡ ባጭሩ ፡ ከመረመርን ፡ በኋላ ፡ የቻርተሩን ፡ አንቀጾች ፡ (ቁጥሮች)፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እንመረምራለን ። ከነዚህ ፡ ውስጥም ፡ በቀጥታ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያላቸውን ፡ ቁጥሮችና ፡ ተጨማሪ ፡ ደጋፊ ፡ ሕግ ፡ ካልወጣ ፡ በቀር ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ሊኖራቸው ፡ የማይችሉትን ፡ ቁጥሮች ፡ ለይተን ፡ ለማመልከት ፡ እንሞክራለን ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

### የተለየ ፡ ጥናት ፡- በአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ ስለተሰጡት ፡ ሥልጣኖች ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### "ቻርተር ፡" ስለሚለው ፡ ቃል ፡ ትርጉምና ፡ አገባብ ።

የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተቋቋመበት ፡ ሕግ ፡ "ቻርተር ፡" እየተባለ ፡ የሚጠራው ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕጎች ፡ በይፋ ፡ (በኦፊሴል) ፡ ታትመው ፡ የሚወጡበትን ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ያቋቋመው ፡ የ፲፱፻፴፭ቱ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ የኢትዮጵያን ፡ መሠረታውያንና ፡ ንዑሳን ፡ ሕጎች ፡ በዝርዝር ፡ ይገልጣል ። ዝርዝሩም ፡ የሚከተሉትን ፡ የሕግ ፡ ዓይነቶች ፡- ማለት ፡ አዋጆችን ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ሕጎችን ፡ ደንቦችን ፡ ውሳኔዎችን ፡ ትእዛዞችን፡ ማስታወቂያዎችን ፡ እና ፡ የነዚህም ፡ የበታች ፡ የሆኑ ፡ ደንቦችን ፡ ይጨምራል[31]።- ቻርተርም ፡ ሆነ ፡ የመንግሥት ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ በዚህ ፡ አዋጅ ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ ተጠቅሶ ፡ አይገኝም ። በዘልማድ ፡ ግን ፡ የኋለኛው ፡ እንደሕግ ፡ መልክ ፡ (ፎርም)፡ ሲያገለግል፡ የፊተኛው ፡ ደግሞ ፡ ላንድ ፡ የሕግ ፡ መልክ ፡ (ፎርም) ፡ አርእስት ፡ እየሆነ ፡ ይወጣል ። ቻርተር ፡ እንደመንግሥት ፡ ማስታወቂያም ፡ ይወጣል ። የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ በመሠረታውያንና ፡ በንዑሳን ፡ ሕጎች ፡ መካከል ፡ የሚገኝ ፡ የሕግ ፡ ዓይነት ፡ ነው ። አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ እንደአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ ያለ ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግ ፡ በመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ መልክ ፡ ይወጣል ፤ (የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፵፱/፲፱፻፵፰ን ፡ ይመለከቷል) ። የመንግሥት ፡ ማስታወቂያዎች ፡ የሚመደቡት ፡

31. ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፴፭ ፡ ቁጥር ፡ ፪(ሀ) ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ አንደኛ ፡ ዓመት ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ።

"ሕጎች" ወይም ፡ "ደንቦች" ፡ በሚሉት ፡ በ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ ፡ ምሕረቱ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር፡ ፩ ፡ ውስጥ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ስር ፡ ሲሆን ፡ የሚመደቡበትም ፡ ክፍል ፡ እንደሚመለከቱት፡ ጉዳይ ፡ ዐቢይነት ፡ ይለያያል ።

በአዋጅም ፡ ሆነ ፡ በድንጋጌ ፡ በትእዛዝ ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ የተቋቋሙ ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ የሚተዳደሩ ፡ አቋሞች ፡ ሁሉ ፡ "ባለቻርተር ፡ ድርጅት" ፡ በመባል ፡ ይታወቃሉ ። የ፲፱፻፶፪ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ፡ ከመታወጁ ፡ አስቀድሞ ፡ መንግሥታዊ ፡ ድርጅቶችና ፡ የግል ፡ ማኅበሮች ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ሆነው ፡ እንዲገሙቱ ፡ ለማድረግ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ቻርተር፡ ይሰጣቸው ፡ ነበር ። የተባሉት ፡ ድርጅቶችና ፡ ማኅበሮች ፡ ከቻርተር ፡ በስተቀር ፡ ሊቋቋሙበት ፡ የሚችሉበት ፡ ሕጋዊ ፡ መሠረት ፡ አልነበረም ። እንደ ፡ ወጣቶች ፡ ወንዶች፡ ክርስቲያናዊ ፡ ማኅበር ፡ (ወወክማ) ፡ ያሉት ፡ የግል ፡ ማኅበሮች ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ የታተመ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ቻርተር ፡ ሊያገኙ ፡ የቻሉት ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከታወጀ[32] ፡ በኋላ ፡ ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በጎ ፡ አድራጎት ፡ ድርጅት ፡ ከተሰጠው ፡ በስተቀር ፡ ለሌላ ፡ ግላዊ ፡ ማኅበርም ፡ ሆነ ፡ ድርጅት ፡ የተሰጠ ፡ ቻርተር ፡ የለም ።

## ምዕራፍ፡፯።

## ስለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ ፎርም ፡ እና ፡ ስለሕጋዊ ፡ ምንጩ ።

የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ የተሰጠው ፡ በመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ መልክ ፡ (ፎርም) ነው ። ከዚህ ፡ በቀደም ፡ ይልቁንም ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከታወጀ ፡ በኋላ ፡ በሕግም ፡ ሆነ ፡ በዘልማድ ፡ ይደረግ ፡ የነበረው ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ የሚተዳደሩ ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ከመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ይልቅ ፡ በትእዛዝ ፡ ማቋቋም ፡ ነበር ። በተጨማሪም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በሚያውጁት ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በጉዳዩ ፡ መክሮ ፡ ሀሳብ ፡ እንደሰጠበት ፡ የሚገለጸው ፡ ሕጉ ፡ በትእዛዝ ፡ ወይም ፡ በድንጋጌ ፡ መልክ ፡ የወጣ ፡ ሲሆን ፡ እንጂ ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ በሚወጣበት ፡ ጊዜ ፡ አልነበረም ። ደራሲው ፡ እንደሚያውቀው ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት፡ በጉዳዩ ፡ መክሮ ፡ ሀሳብ ፡ መስጠቱን ፡ ሳይጠቅሱ ፡ ያለፉ ፡ በትእዛዝ ፡ መልክ ፡ የወጡ፡ ሕጎች ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ማስተዳደሪያ ፡ ጠቅላይ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ትእዛዝ፡ (ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፩/፲፱፻፶፬) ፡ እና ፡ የሚኒስትሮች ፡ ሥልጣን ፡ ማሻሻያ ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ እና ፡ ፪ ፡ (ማለት ፡ የ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፵፬ ፡ እና ፡ ፵፮፡) ናቸው ። እንግዲህ ፡ የአዋሽን ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሚያቋቁመው ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቁጥር ፡ ፪፻፺፱/፶፬ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤትም ፡ በጉዳዩ ፡ መክሮ ፡ ሀሳብ ፡ እንደሰጠበት ፡ መጥቀሱ ፡ ያልተለመደ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ደራሲው ፡ ባደረገው ፡ መከታተል ፡ በመጀመሪያ ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ረቂቅ ፡ በትእዛዝ ፡ መልክ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ እንደነበረና ፡ ሊወጣ ፡ የታሰበበትም ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ፡ ሥልጣን ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ መሆኑ ፡ መጠቀሱን ፡ ደርሶበታል ። በዚህም ፡ መከታተል ፡ መሠረት ፡ ራሳቸውን ፡ ችለው ፡ የሚተዳደሩ ፡ ድርጅቶችን ፡ ሁሉ ፡ በቻርተር ፡ ማቋ

---

32. የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፬፻፬ - ፬፻፹፪ ፡ መሠረት ፡ ተቋቁመው ፡ ለተመዘገቡ ፡ የግል ፡ ማኅበሮች ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ይሰጣቸዋል ።

ቋም ፡ ጥንቱንም ፡ የተለመደ ፡ መሆኑን ፡አርቃቂው ፡ በማስታወስ ፡ ለረቂቁ ፡ "ቻርተር" የሚል ፡ አርእስት ፡ የሰጠው ፡ ይመስላል ።[33] "የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤታችን ፡ የመከረበትን ፡ ዓይተንና ፡ ፈቅደን ፡" የሚሉት ፡ ቃላት ፡ ሕጉ ፡ መጀመሪያውኑ ፡ በትእዛዝ ፡ መልክ ፡ ሲዘጋጅ ፡ በቀዳሚው ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩ ፡ ሲሆኑ ፡ ኋላም ፡ የሕጉ ፡ መልክ ፡ ከትእዛዝ ፡ ወደመንግሥት ፡ ማስታወቂያነት ፡ ሲለወጥና ፡ አንቀጽ ፡ ፳፺ን ፡ የሚጠቅሰው ፡ ቃል ፡ ሲሠረዝ ፡ እንዳሉ ፡ ቀርተዋል ።

በደራሲው ፡ አስተያየት ፡ ሕጉን ፡ በትእዛዝ ፡ ከማውጣት ፡ ይልቅ ፡ በመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ መልክ ፡ ማውጣት ፡ የተሻለ ፡ መሆኑን ፡ የመንግሥቱ ፡ የአስፈጻሚው፡ ክፍል ፡ የመረጠበት ፡ ምክንያት ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ በመከተል ፡ በትእዛዝ ፡ አማካይነት ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሊሰጥ ፡ ከሚችለው ፡ ሥልጣን ፡ ይልቅ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ ቻርተር ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችለው ፡ ሥልጣን ፡ የሰፋና ፡ የላቀ ፡ እንደሆነ ፡ አድርጎ ፡ ስላመነበት ፡ ይመስላል ።

ሕጉ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፺ን ፡ ባይጠቅስም ፡ መልኩም ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ እንጂ ፡ ትእዛዝ ፡ ባይሆንም ፡ የጥንቱ ፡ ረቂቅ ፡ በትእዛዝ ፡ መልክ ፡ ስለሆነ ፡ የሕጉን ፡ መግቢያ ፡ ቃላት ፡ በተለይም ፡ "የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤታችን ፡ የመከረበትን---" የሚሉትን ፡ በመመልከት ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ የወጣው ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፺ ፡ በተመለከተው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ይመስላል ። መልኩ ፡ "ትእዛዝ" ፡ አለመሆኑ ፡ ብቻ ፡ ሕጉን ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ የሚቃረን ፡ ወይም ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ ፈራሽ ፡ አያደርገውም ።[34]

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

## የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ ሕጋዊ ፡ ምርምር ።

ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ ከአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ ውስጥ ፡ አሁኑኑ ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያላቸውንና ፡ ወደፊት ፡ ተጨማሪ ፡ ደጋፊ ፡ ሕግ ፡ ካልወጣ ፡ በቀር ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ሊኖራቸው ፡ የማይችሉትን ፡ ቁጥሮች ፡ በመለየት ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፺ ፡ መሠረት ፡ ለባለሥልጣኑ ፡ የተሰጡትን ፡ ሥልጣኖች ፡ እንመርምር ።

### ሀ/ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ተግባር ፤

የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ጠቅላላ ፡ ተግባር ፡ በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፬ ፡ በመጀመሪያው ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ እንደሚከተለው ፡ ተደንግጎ ፡ ይገኛል ።

"የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ዋና ፡ ተግባር ፡ የአዋሽን ፡ ሸለቆ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶች ፡ ለማስተዳደርና ፡ ለማልማት ፡ ነው ።"

እዚህ ፡ ላይ ፡ መታወስ ፡ ያለበት ፡ "ተግባር" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ኃላፊነትንም ፡ ተግባርንም ፡ አጠቃሎ ፡ እንዲይዝ ፡ ተደርጎ ፡ የገባ ፡ መሆኑን ፡ ነው ።

---

33. ቻርተሩ ፡ ሲዘጋጅ ፡ ዋናው ፡ አርቃቂ ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሊሰጡ ፡ ታቅደው ፡ ከነበሩት ፡ ሥልጣኖች ፡ ውስጥ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ሊሰጡ ፡ የሚችሉት ፡ በአዋጅ ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ አመልክተው ፡ እንደነበር ፡ የሚያስረዳ ፡ ማስረጃ ፡ አለ ።
34. ጄምስ ፡ ሲ ፡ ኤን ፡ ፖል ፡ ኬዝስ ፡ ኤንድ ፡ ማቴሪያልስ ፡ ኦን ፡ ፐብሊክ ፡ ሎ ፡ ዋን ፡ (፲፱፻፷፯ - ፲፱፻፷፰) (ያልታተመ)፡ የሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት ፡ ቀ፡ኃ ፡ ሥ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፫ ፡ ገጽ ፡ ፭፫ ።

ለ/ በዝርዝር ፡ ስለተመለከቱት ፡ የባለሥልጣኑ ፡ ተግባሮች ፤

በቁጥር ፡ ፬ ፡ ውስጥ ፡ ከተደነገገው ፡ እና ፡ በተከታዮቹም ፡ የቻርተሩ ፡ ቁጥሮች ፡ ካል ተወሰነው ፡ ጠቅላላ ፡ ተግባር ፡ ሌላ ፡ ከቁጥር ፡ ፬(ሀ) እስከ ፡ (ቀ) ፡ የተመለከቱት ፡ ተግባሮችም ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተሰጡ ፡ ናቸው ። ከነዚህ ፡ አንዳ ንዳቹ ፡ ተግባሮች ፡ ልዩ ፡ ምርመራ ፡ አያስፈልጋቸውም ።

የተለየ ፡ ምርመራ ፡ የሚያሻቸው ፡ ሁለቱ ፡ ቁጥሮች ፡ የሚከተሉትን ፡ ጉዳዮች ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ።

፩/ የአዋሽን ፡ ውሀ ፡ መቆጣጠርና ፡ ማከፋፈል ፤

(፩) የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፬(ረ) ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የአዋሽን ፡ ወን ዝ ፡ ውሀዎች ፡ ለመስኖና ፡ ለሌላም ፡ ጉዳይ ፡ ለማከፋፈል ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የተ ለየ ፡ የግል ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል ። ይህ ፡ ቁጥር ፡ በአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ውሀዎች ፡ እንደመንግሥት ፡ ንብረት ፡ አድርጎ ፡ ይገምታቸዋል ። በተሻሻ ለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴ ፡ መሠረት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶች ፡ ውሀዎች ፡ ሀይቆችና ፡ ወንዞችም ፡ ጭምር፡ በመንግሥት ፡ ንብረት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብቶች ፡ ሆነዋል ። በ፲፱፻፶፪ቱም፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፪፻፳፫ ፡ እና ፡ ፩ሺ፬፻፵፯ ፡ የፈሳሽና ፡ የረጋ ፡ ውሀ ፡ ሁሉ ፡ ባለሀብትነት ፡ የመንግሥት ፡ ሲሆን ፡ ኅብረት ፡ ሰቡ ፡ በተጠቃ ሰው ፡ ውሀ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ መብት ፡ የተጠቃሚነት ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ ይደነግጋሉ ። በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፪፻፳፬ ፡ ውስጥ ፡ እንደተመለከተው ፡ ውሀ ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ተብሎ ፡ የሚገመተው ፡ በሰው ፡ ሠራሽ ፡ ውሀ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ በኩሬ ፡ ጉድጓድ ፡ ወይም ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ውስጥ ፡ የተከማቸ ፡ የሆነ ፡ እና ፡ እንደተፈጥሮውም፡ መፍሰስ ፡ ሳይቻለው ፡ የቀረው ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ቁጥር ፡ ፩ሺ፪፻፳፫ ፡ (፪) ፡ ፈሳሽና ፡ የረጋ ፡ ውሀ ፡ ሁሉ ፡ አግባብ ፡ ባለው ፡ ባለሥልጣን ፡ ቁጥጥርና ፡ ጥበቃ ፡ ስር ፡ እንዲሆን፡ ያዛል ። በተጨማሪም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ በቁጥር ፡ ፩ሺ፪፻፴ ፡ (፫) ስር ፡ በጠ ቅላላም ፡ ሆነ ፡ ለአንድ ፡ የተለየ ፡ ቀበሌ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያላቸው ፡ ልዩ ፡ ሕጎችና ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ ደንቦች ፡ የተጠበቁ ፡ መሆናቸውን ፡ ይደነግጋል ። የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ አንድ ፡ የተለየ ፡ ቀበሌን ፡ የሚመለከት ፡ የተለየ ፡ ሕግ ፡ ስለሆነ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከቱት ፡ ውሀን ፡ የሚመለከ ቱት ፡ ቁጥሮች ፡ ሁሉ ፡ በባለሥልጣኑ ፡ ላይ ፡ ተፈጻሚነት ፡ አይኖራቸውም ። ይህ ፡ ግን ፡ ሊሆን ፡ የሚችለው ፡ ባለሥልጣኑ ፡ በሌላ ፡ አግባብ ፡ ባለው ፡ ደጋፊ ፡ ሕግ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶት ፡ ሲገኝ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የአዋሽን ፡ ወንዝ ፡ ውሀዎች ፡ ለመስኖና ፡ ለሌላም ፡ ጉዳይ ፡ ለማዋል ፡ ለሚሹ ፡ አስፈላጊውን ፡ አሟልተው ፡ ለሚገኙ ፡ ሁሉ ፡ ውሀ ፡ እንዲያከፋፍል ፡ ለአ ዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ያለአድልዎና ፡ ማማረጥ ፡ የተከና ወነ ፡ ከሆነ ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያለው ፡ ይሆናል ።

(፪) የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፱ ፡ በመንግሥቱ ፡ ማንኛውም ፡ ቅርንጫፍ ፡ እና ፡ በተጠ ቃሚዎች ፡ መካከል ፡ በተደረገ ፡ ስምምነት ፡ አማካይነት ፡ የተሰጠ ፡ በአዋሽ ፡ ሸለቆ፡ ውሀዎች ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ የመጠቀም ፡ መብት ፡ የተጠበቀ ፡ መሆኑን ፡ ይደነግጋል ። ይህ፡ ቁጥር ፡ ታስቦ ፡ የተጨመረ ፡ ሲሆን ፡ ኤች ፡ ቪ ፡ ኤ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅ በር ፡ (ወንጂ) ፡ በስምምነት ፡ መሠረት ፡ ያገኘውን ፡ በውሀ ፡ የመጠቀም ፡ መብት ፡ ለመ ጠበቅ ፡ ነው ። የዚህ ፡ ቁጥር ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ በስምምነት ፡ መሠረት ፡ የተገኙትን ፡ አስ

ቀድመው ፡ የነበሩትን ፡ መብቶች ፡ ለመጠበቅና ፡ በተጠቃሚዎችም ፡ መካከል ፡ ማማረጥና ፡ አድልዎ ፡ እንዳይደረግ ፡ ለመከላከል ፡ ነው ። የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የመንግሥት ፡ ወኪል ፡ በመሆን ፡ በስምምነት ፡ የተገኙ ፡ መብቶችን ፡ በማክበር ፡ በሚያስተዳድረው ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ውሀ ፡ አጠቃቀም ፡ የመቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

<u>፪/ የአዋሽን ፡ ሸለቆ ፡ ሀብት ፡ በበለጠ ፡ ለማልማት ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ስለማድረግ ፤</u>

የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፬ (ቀ) ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሸለቆውን ፡ ሀብት ፡ በበለጠ ፡ ለማልማትና ፡ ለአገልግሎት ፡ ለማዋል ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ እንዲያደርግ ፡ ጠቅላላ ፡ ኃላፊነት ፡ ይጥልበታል ።

ይህን ፡ ቁጥር ፡ በመመርኰዝ ፡ ባለሥልጣኑ ፡ በአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ግድብ ፡ በማሠራት ፡ የወንዙን ፡ የተፈጥሮ ፡ አወራረድ ፡ የሚለውጥ ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፤ ወራጁን ፡ ውሀ ፡ ገድቦ ፡ ለማጠራቀም ፡ ወይም ፡ ውሀውን ፡ በማቃናት ፡ እና ፡ መንገዱን ፡ በመለወጥ ፡ አንዳንድ ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ ቀበሌዎች ፡ እንዲለሙ ፡ ለማድረግ ፡ ይችላል ። ባለሥልጣኑ ፡ እነዚህን ፡ እና ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆኑ ፡ እቅዶችን ፡ በሚያከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ እቅዱ ፡ ከሚከናወንበት ፡ ስፍራ ፡ ዝቅ ፡ ብለው ፡ የሚገኙ ፡ የወንዙን ፡ ውሀ ፡ ለቤት ፡ ውስጥና ፡ ለመስኖ ፡ እንዲሁም ፡ ለኢንዱስትሪ ፡ የሚያውሉ ፡ ሰዎችን ፡ መብት ፡ ይነካ ፡ ይሆናል ። የቀረው ፡ ቢቀር ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተው ፡ እንዲህ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ የመጠቀም ፡ መብት ፡ እንደሚከበር ፡ ወይም ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ከታች ፡ የሚገኙ ፡ ተጠቃሚዎችን ፡ መብት ፡ እንደሚያከብር ፡ ተደርጎ ፡ መተርጐም ፡ አለበት ።

<u>ሐ/ ለባለሥልጣኑ ፡ ስለተሰጡ ፡ ተራ ፡ ሥልጣኖች ፤</u>

በቻርተሩ ፡ ቁጥሩ ፡ ፰ ፡ የተሰጡት ፡ ሥልጣኖች ፡ የሕግ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ማንኛውም ፡ ድርጅት ፡ ሊኖሩት ፡ የሚችሉ ፡ ሥልጣኖች ፡ ናቸው ። እነዚህም ፡ ውል ፡ የመዋዋልን ፡ በራስ ፡ ስም ፡ የመከሰስ [35] ፡ ወይም ፡ የመክሰስን ፡ ንብረት ፡ የማደርጀትን ፡ ለንብረት ፡ ባለቤት ፡ የመሆንንና ፡ ንብረትን ፡ እንደፈቀዱ ፡ የማድረግን ፡ ሥልጣን ፡ ይጨምራሉ ።

በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ የወጣ ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ እንደተጠቀሱት ፡ የአስፈጻሚ ፡ ክፍል ፡ ሕጎች ፡ ይቆጠራልን ? የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ ሚስተር ፡ ፓጉስኪ ፡ [36] የተባሉ ፡ ሕግ ፡ አዋቂ ፡ በሰፊው ፡ ከመረመሩ ፡ በኋላ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ የወጣ ፡ ማስታወቂያ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ከተጠቀሱት ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ሕጎች ፡ ጋር ፡ የማይመሳሰል ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ አስተያየት ፡ ሰጥተዋል ። ይህም ፡ እውነት ፡ ከሆነ ፡ የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፰ ፡ ለአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ የሚጠቅም ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሰጥቶታል ። የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣንም ፡ እንደግል ፡ ድርጅት ፡ በመሆን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በተሰጡት ፡ የሰውነት ፡ መብቶች ፡ የሚጠቀመው ፡ በሚኒስቴ

---

35. "SUE" እና ፡ "SUED" በሚሉት ፡ ፈንታ ፡ "USE" እና ፡ "USED" የሚሉት ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቃላት ፡ በቁጥር ፡ ፰(ለ) ፡ እንግሊዘኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ይገኛሉ ። ይህ ፡ በእርግጥ ፡ የእትም ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

36. አር ፡ ጂ ፡ ኤች ፡ ፓጉስኪ ፡ <u>ፕረሊሚኔሪ ፡ አናሊሲስ ፡ አፍ ፡ ዘ ፡ ቻርተር ፡ አፍ ፡ ኤ. ቪ. ኤ</u> ፡ (፲፻፷፱፻፷፯) (ያልታተመ) ገጽ ፡ ፬ ።

ሮች ፡ ወይም ፡ በሌሎች ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ስም ፡ እንጂ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ ቢሆንም ፡ ከመንግሥቱ ፡ የተለየ ፡ አቋም ፡ ስላለው ፡ በተሰጡት ፡ የግል ፡ መብቶች ፡ አይደለም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ደራሲው ፡ የሚስተር ፡ ፓጉስኪን ፡ አስተያየት ፡ የሚቀበልበት ፡ ምክንያት ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እንጂ ፡ በፍትሐ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሰ ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ድርጅት ፡ ባለመሆኑንና፡ የሚጠቀመውም ፡ ከአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ በወጣ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በተመለከቱ ፡ መብቶች ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በተመለከቱት ፡ የሰውነት ፡ መብቶች ፡ የሚጠቀመው ፡ ጉዳዩ ፡ በሚመለከታቸው፡ ሚኒስቴሮችና ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ስም ፡ ለመሆኑ ፡ "ጉዳዩ ፡ ከሚመለከታቸው ፡ ጋር ፡ በመተባበር" ፡ "የመንግሥት ፡ ወኪል ፡ በመሆን" ፡ "የመንግሥት ፡ ሚኒስቴሮችና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ወኪል ፡ በመሆን ፡" የሚሉት ፡ የባለሥልጣኑን ፡ የተለዩ ፡ ሥልጣኖች ፡ የሚወስኑት ፡ የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ ቃላት ፡ እንደማስረጃ ፡ ሊቀርቡ ፡ ይችላሉ ። ባለሥልጣኑ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ መብቶች ፡ የሚጠቀመው ፡ ቁጥር ፡ ፫፻፺፪ ፡ ውስጥ ፡ በተመለከቱት ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ሕጎች ፡ አለመሆኑን፡ ይገነዘቧል ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ስለ ፡ ባለሥልጣኑ ፡ የተለዩ ፡ ሥልጣኖች ፡ በሚደነግገው ፡ የቻርተሩ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ቢገኙም ፡ የሚከተሉት ፡ ሥልጣኖች ፡ ማለት ፡ የመንግሥት ፡ ወኪል ፡ በመሆን ፡ የኢንተርናሺናል ፡ እርዳታዎችና ፡ ብድሮች ፡[37] ተቀብሎ ፡ በሥራ፡ ላይ ፡ የማዋል ፡ ሥልጣን ፡ (ቁጥር ፡ ፯ (ረ)) ፡ በአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ የመንግሥት ፡ ሚኒስቴሮችና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሥራዎች ፡ ወኪል ፡ ሆኖ ፡ የማካሄድ ፡ ሥልጣን ፡ (ቁጥር ፡ ፯ (ሰ)) ፤ በአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ የመሬት ፡ ባለቤትነት ፡ ሁኔታ ፡ የማጣራትና ፡ የመንግሥትም ፡ የሆነውን ፡ መሬት ፡ የማስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ (ቁጥር ፡ ፰) ፤ የአዋሽን ፡ ሸለቆ ፡ በሚገባና ፡ በኢኰኖሚ ፡ ረገድ ፡ በሚጠቅም ፡ አኳኋን ፡ ለማልማት ፡ በቻርተሩ ፡ ውስጥ ፡ የተሰጡትን ፡ ሥራዎች ፡ የመፈጸም ፡ ሥልጣን ፡ (ቁጥር ፡ ፱) ፤ እና ፡ ከቻርተሩ ፡ ጋር ፡ የሚስማሙትን ፡ የውስጥ ፡ ደንቦች ፡ የማውጣት ፡ ሥልጣን ፤ ሁሉ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ክርክር ፡ ሊያስነሱ ፡ የማይችሉና ፡ በሚገባ ፡ የተሰጡ ፡ ሥልጣኖች ፡ ናቸው ።

**መ/ ለባለሥልጣኑ ፡ ስለተሰጡት ፡ የተለዩ ፡ ሥልጣኖች ፤**

ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተሰጡትን ፡ የተለዩ ፡ ሥልጣኖች ፡ እንደሚከተለው ፡ ከፋፍለን ፡ በየተራ ፡ በመተንተን ፡ እንመረምራለን ።

**(፩) የመቆጣጠር ፡ ሥልጣኖች ፤**

እዚህ ፡ ላይ ፡ አከራካሪዎቹ ፡ ጥያቄዎች ፡-

ሀ/ ቻርተሩ ፡ ለባለሥልጣኑ ፡ የመቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፡ ሲሰጥ ፡ ተገቢው ፡ መንግሥታዊ ፡ ድርጅት ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለሆነ ፡ በተባለው ፡ የመቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፡ ሊጠቀም ፡ ይገባል ፡ በሚል ፡ አስተሳሰብ ፡ በመመራት ፡ በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ሥራ ፡ ማደላደሉ ፡ ነው? ወይስ ፡

37. ዋናው ፡ የቻርተሩ ፡ አርቃቂ ፡ እንደገለጹት ፡ የቻርተሩ ፡ አንቀጽ ፡ ፯(ረ) ፡ የታቀደው ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ በብድር ፡ የተገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ እንጂ ፡ ለብድሩ ፡ ኃላፊ ፡ እንዲሆን ፡ አልነበረም ። እንዲያውም ፡ የብድሩ ፡ ውል ፡ የሚፈጸመው ፡ አግባብ ፡ ባለው ፡ በሌላ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ነው ።

ለ/ ቻርተሩ ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሚሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ አዲስና ፡ መንግሥቱም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በተራው ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ያልነበረውን ፡ ሥልጣን ፡ ነው ? የሚሉ ፡ ናቸው ።

እነዚህን ፡ ጥያቄዎች ፡ መመሪያ ፡ በማድረግ ፡ የመቆጣጠርን ፡ ሥልጣን ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሚሰጡትን ፡ የሚከተሉትን ፡ በዝርዝር ፡ የተጠቀሱትን ፡ የቻርተሩን ፡ ቁጥሮች ፡ ጠልቀን ፡ እንመረምራለን ። "የመቆጣጠር ፡ ሥልጣን" ስንል ፡ በሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ማለት ፡ በተራ ፡ ዜጎች ፡ ላይ ፡ የተሰጠ ፡ የመንግሥቱንና ፡ የአዋሽን ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ውስጣዊ ፡ አስተዳደር ፡ የማይመለከት ፡ ሥልጣን ፡ ማለታችን ፡ ነው ።

(ሀ) <u>ንብረቶችን ፡ የማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፤</u>

የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፯(ሀ) ፡ በሕግ ፡ በሚወሰነው ፡ መሠረት ፡ ከግል ፡ ባለቤቶች ፡ በማስለቀቅ ፡ የማይንቀሳቀሱና ፡ ሌሎችንም ፡ ንብረቶች ፡ ለማግኘት ፡ እንዲችል ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተለየ ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል ።

ይህም ፡ ቁጥር ፡ "ሕግ"፡ ሲል ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ ውስጥ ፡ ተጠቅሶ ፡ የሚገኘውን ፡ ስለግል ፡ ንብረቶች ፡ መወሰድ ፡ (ኤክስፕሮፕሪዬሽን) ፡ በተለይ ፡ የሚወጣውን ፡ ሕግ ፡ መሆኑን ፡ ደራሲው ፡ ያምንበታል ። ይህ ፡ ስለ ፡ ግል ፡ ንብረቶች ፡ መወሰድ ፡ በተለይ ፡ እንዲወጣ ፡ የታቀደው ፡ ሕግ ፡ በ፲፱፻፶፪ቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከቍጥር ፡ ፲፬፻፷ ፡ እስከ ፡ ፲፬፻፹፰ ፡ ባሉት ፡ ውስጥ ፡ ተመልክቶ ፡ ይገኛል ። በቍጥር ፡ ፲፬፻፷ ፡ መሠረት ፡ ንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡ ማለት ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ አገልግሎት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ ሁሉ ፡ ባለሀብት ፡ እንዲለቅ ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ የሚያስገድድበት ፡ ሥርዓት ፡ ነው ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፲፬፻፷፩ ፡ "ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ አገልግሎት፡" የሚለውን ፡ ሀሳብ ፡ በማብራራት ፡ አንድ ፡ ሀብት ፡ ከመወሰዱ ፡ በፊት ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከታቸው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ አስቀድሞ ፡ ሀብቱ ፡ እንዲወሰድ ፡ ያስፈለገው ፡ ዕቅድ ፡ ለሕዝብ ፡ ጠቃሚ ፡ መሆኑን ፡ እንዲወስኑ ፡ ያዛል ። እንዲያውም ፡ "ፓብሊክ ፡ ዩቲሊቲ፡" (ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ የዋለ ፡ ነገር) ፡ "ፓብሊክ ፡ ኢንተረስት ፡" (ለሕዝብ ፡ የሚጠቅም ፡ ነገር) ፡ እና ፡ "ፓብሊክ ፡ ፐርፐስ ፡" (የሕዝብን ፡ ጥቅም ፡ የሚመለከት ፡ ነገር) ፡ የሚሉት ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቃላት ፡ በመለዋወጥና ፡ በተመሳሳይነት ፡ አግባብ ፡ ባለው ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ተመልክተው ፡ ይገኛሉ ።

አንድ ፡ ዕቅድ ፡ ለሕዝብ ፡ አስፈላጊ ፡ ወይም ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ መሆን ፡ ወይም፡ አለመሆኑ ፡ የሚለካው ፡ ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ሊውል ፡ የተዘጋጀ ፡ ሊውል ፡ የሚችልና ፡ ሊውልም ፡ የታሰበ ፡ መሆኑ ፡ ሲረጋገጥ ፡ ብቻ ፡ ነው ። እርግጥ ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ተግባር ፡ ይህን ፡ አሟልቶ ፡ ይገኛል ። ምንም ፡ እንኳ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፲፬፻፷፩(፩) ፡ "ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ የሚውል ፡" ነገር ፡ የሚለውን ፡ አስተሳሰብ ፡ ሲወስን ፡ የንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡ ግቡ ፡ ገንዘብ ፡ ማግኘት ፡ ብቻ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡ አይቻልም ፤ ቢልም ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ በአማርኛውና ፡ በረቂቁ ፡ ቋንቋ ፡ በፈረንሳይኛው ፡ (የእንግሊዝኛው ፡ የተለየ ፡ ቢሆንም) ፡ "ስለሆነም" ፡ በማለት ፡ በንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፩ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተውን ፡ አሻሽሎታል።

ስለዚህ ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ተገቢ ፡ የሆነውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በመከተል ፡ የግል ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረት ፡ በማስለቀቅ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚውሉ ፡ ዕቅዶችን ፡ ካሠራ ፡ በኋላ ፡ የመሬት ፡ ዋጋ ፡ ከፍ ፡ እንዲል ፡ ምክንያት ፡ በመሆን ፡ ከሚገኘው ፡ ጥቅም ፡ ሕዝቡ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆን ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ። ግድቦችና ፡

የመስኖ ፡ ውሃ ፡ መተላለፊያ ፡ ቦዮች ፡ በግልጽ ፡ ለሕዝብ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጡ ፡ ዕቅዶች ፡ በመሆናቸው ፡ ለነዚህ ፡ መሥሪያ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ለጊዜው ፡ በሚገባ ፡ ለምቶ ፡ የማይገኘውን ፡ መሬት ፡ ለማስለቀቅና ፡ በልማት ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ማድረግ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፩ሺ፱፻፷፬(፪) ፡ የተደገፈ ፡ ሕጋዊ ፡ እርምጃ ፡ ነው ። ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ለማዋል ፡ ሲባል ፡ የግል ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ ማስለቀቅ ፡ እንደሚቻል ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የአንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ የአማርኛው ፡ ቃል ፡ በግልጽ ፡ ቢደነግግም ፡ "ለሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡" የሚሉት ፡ የአማርኛው ፡ ቃላት ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ውስጥ ፡ ተመሳሳይ ፡ የላቸውም ።

እንግዲህ ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ በቁጥር ፡ ፯ ፡ ውስጥ ፡ "ሕግ ፡ በሚወስነው ፡ መሠረት ፡" ሲል ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ስለግል ፡ ንብረቶች ፡ ማስለቀቅ ፡ በተለይ ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ እና ፡ ሌሎችም ፡ እሱን ፡ ለማስፈጸም ፡ የወጡት ፡ ሕጎች ፡ በሚወስኑት ፡ መሠረት ፡ ማለቱ ፡ ከሆነ ፡ በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፯(ሀ) ፡ ለባለሥልጣኑ ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ሕጋዊና ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያለውም ፡ ነው ። ግን ፡ "ሕግ፡" ሲል ፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተውን ፡ ስለግል ፡ ንብረቶች ፡ ማስለቀቅ ፡ በተለይ ፡ የወጣውን ፡ ሳይሆን ፡ አግባብ ፡ ያለውን ፡ ማንኛውንም ፡ ሌላ ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ሕግ ፡ ማመልከቱ ፡ ከሆነ ፡ በተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ የተሰጠው ፡ የንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡ ሥልጣን ፡ ሕጋዊ ፡ እንዲሆንና ፡ ተፈጻሚነትም ፡ እንዲኖረው ፡ ስለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ በአግባቡ ፡ ማውጣት ፡ ይገባል ። ምክንያቱም ፡ የንብረት ፡ ማስለቀቅ ፡ ሥልጣንን ፡ ለመስጠት ፡ የሚቻለው ፡ በአዋጅ ፡ ወይም ፡ በድንጋጌ ፡ መልክ ፡ በወጣ ፡ ሕግ ፡ አማካይነት ፡ ብቻ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

(ለ) የአዋሽን ፡ ሸለቆ ፡ ውሀና ፡ መገልገያዎች ፡ አጠቃቀም ፡ የመቆጣጣጠር ፡ ሥልጣን ፤

የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ውሀ ፡ መሬትና ፡ እንዲሁም ፡ ሌሎች ፡ ነገሮች ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ የሚውሉበትን ፡ ሥርዓት ፡ የሚደነግግ ፡ ደንብ ፡ ለማውጣት ፡ እንዲችል ፡ የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፬(ሠ) ፡ እና ፡ ፯(መ) ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጡታል ።

ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ የመንግሥቱ ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ባለሥልጣን ፡ ፈሳሽንና ፡ የረጋን ፡ ውሀ ፡ ሁሉ ፡ የመቆጣጠር ፡ እና ፡ የመከባከብ ፡ ግዴታና ፡ ሥልጣን ፡ ያለበት ፡ መሆኑን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፸፰(፪) ፡ እንደሚወስን ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ ገልጠናል ። በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ ውስጥ ፡ እንደተመለከተው ፡ ሁሉ ፡ በአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ላይ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ ቀበሌ ፡ ውስጥ ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ የመንግሥቱ ፡ የአስፈጻሚ ፡ ክፍል ፡ ይኸው ፡ ባለሥልጣን ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ባለሥልጣኑ ፡ የሚያወጣቸውና ፡ በሚያስተዳድረው ፡ ቀበሌ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያላቸው ፡ የአዋሽን ፡ ወንዝ ፡ ውሀ ፡ ተጠቃሚዎች ፡ የሚመለከቱ ፡ ደንቦች ፡ ሁሉ ፡ በ፲፱፻፶፪ቱ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፱፻፸፩(፫) ፡ መሠረት ፡ ሕጋዊ ፡ እና ፡ የሚጸኑም ፡ ናቸው ። በኃላፊነቱ ፡ ሥር ፡ የሚገኙትን ፡ ሌሎች ፡ መገልጋዮች ፡ ለመቆጣጠር ፡ የሚያስችል ፡ ደንብ ፡ በማውጣት ፡ ረገድ ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ክርክር ፡ ሊያስነሳ ፡ የሚችል ፡ አይደለም ። ምክንያቱም ፡ ማንኛውም ፡ የመንግሥቱ ፡ ክፍል ፡ በኃላፊነቱ ፡ ስር ፡ የሚገኘውን ፡ መገልገያ ፡ ሁሉ ፡ መቆጣጠሩ ፡ ተገቢ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

አስቸጋሪው ፡ ጥያቄ ፡ በቀበሌው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ መሬት ፡ ለመቆጣጠር ፡ የሚያስችል ፡ ደንብ ፡ በማውጣት ፡ ረገድ ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተሰጠው

ሥልጣን ፡ ሊመለከት ፡ የሚችለው ፡ የመንግሥትን ፡ መሬት[38] ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ የግል ፡ መሬትንም ፡ ጭምር ፡ ነው? የሚለው ፡ ነው ።

የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ በቻርተሩ ፡ ውስጥ ፡ ለተዘረዘሩት ፡ ጉዳዮች ፡ በልዩ ፡ ሥልጣን ፡ የሚሠራባቸው ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ወሰኖች ፡ በጂኦግራፊ ፡ እንደ ፡ ተደነገገው ፡ የአዋሽን ፡ ወንዝ ፡ ቀበሌ ፡ እንደሚጠቀልሉ ፡ የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ ያመለክታል ። ስለዚህም ፡ በቻርተሩ ፡ የተመለከተው ፡ የመቆጣጣር ፡ ሥልጣን ፡ ሊመለከት ፡ የሚችለው ፡ የመንግሥት ፡ ንብረት ፡ የሆነውን ፡ መሬት ፡ ብቻ ፡ አይመስልም ። የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ የተፈጥሮ ፡ ኃብት ፡ ሁሉ ፡ ለማስተዳደርና ፡ ለማልማት ፡ ስለሆነ ፡ (ቁጥር ፡ ፬) ፡ በአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ መሬትን ፡ ሁሉ ፡ የአጠቃቀም ፡ ሁኔታ ፡ የሚወስን ፡ ደንብ ፡ ለማውጣት ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ይመስላል ። ደራሲው ፡ እንደሚያውቀው ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተውን ፡ የማንኛውንም ፡ ሰው ፡ ንብረት ፡ የማበጀትና ፡ በፈቀደው ፡ የማዋል ፡ መብት ፡ የሚወስን ፡ ሕግ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ አልወጣም ። የአንቀጽ ፡ ፵፬ ፡ የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ከእንግሊዝኛው ፡ ይልቅ ፡ ግልጽ ፡ ሲሆን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ የተወሰነውን ፡ ሳይተላለፍ ፡ ንብረት ፡ ለማበጀትና ፡ በፈቀደው ፡ ለማዋል ፡ መብት ፡ እንዳለው ፡ ይደነግጋል ። "በሕግ ፡ የተወሰነውን ፡ ሳይተላለፍ ፡" ሲል ፡ በዚያው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ፓርላማ ፡ የሚያወጣውን ፡ ሕግ ፡ ሳይተላለፍ ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

እንዲህ ፡ ያለ ፡ በግል ፡ መሬት ፡ እንደልብ ፡ የመጠቀም ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ነፃነት ፡ ስላለና ፡ ሌላም ፡ ይህንኑ ፡ መብት ፡ የሚወስን ፡ ፓርላማ ፡ ያወጣው ፡ ሕግ ፡ ስለሌለ ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ስለ ፡ ግል ፡ መሬት ፡ አጠቃቀም ፡ ምክር ፡ ሊሰጥ ፡ ይችል ፡ እንደሆነ ፡ እንጂ ፡ የአጠቃቀሙን ፡ ሁኔታ ፡ በሕግ ፡ መልክ ፡ ለመቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ፤ ሊኖረውም ፡ አይችልም ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ በቻርተሩ ፡ ፲(መ) ፡ የተመለከተው ፡ ለባለሥልጣኑ ፡ የተሰጠው ፡ በቀበሌው ፡ የሚገኘውን ፡ መሬት ፡ አጠቃቀም ፡ ሁኔታ ፡ በደንብ ፡ ወስኖ ፡ የማውጣቱ ፡ ሥልጣን ፡ ተጨማሪ ፡ ሕጋዊ ፡ እርምጃ ፡ ካልተወሰደበት ፡ ተፈጻሚነት ፡ ያለው ፡ አይመስልም ። የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ደንብ ፡ በማውጣት ፡ በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፲ ፡ መሠረት ፡ የመንግሥት ፡ መሬት ፡ የያዙ ፡ ሚኒስቴሮችና ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ያስተላለፉለትን ፡ መሬት ፡ እና ፡ በኪራይ ፡ የተሰጠውም ፡ የመንግሥት ፡ መሬት ፡ የሚተዳደርበትን ፡ የአጠቃቀም ፡ ሁኔታ ፡ ሊወስን ፡ ይችላል ።

ማንኛውም ፡ አፈጻጸም ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፯ ፡ ፴፰ ፡ እና ፡ ፵፫ ፡ ዋስትና ፡ የተሰጣቸው ፡ መብቶች ፡ ሁሉ ፡ መከበር ፡ አለባቸው ። በአንቀጽ ፡ ፲(መ) ፡ በመመራት ፡ ባለሥልጣኑ ፡ ከሚያወጣቸው ፡ ደንቦች ፡ ማንኛውም ፡ ቢሆን ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ሕገ ፡ መንግሥታውያን ፡ መብቶች ፡ የማያከብር ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ ዋጋ ፡ የሌለ ውና ፡ የማያገለግል ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ ይገባዋል ።

38. በመንግሥት ፡ ሀብትና ፡ በግል ፡ ሀብት ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ "በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፴ ፡ መሠረት ፡ መንግሥት ፡ በተፈጥሮ ፡ ሀብቶች ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ባለ ፡ ሀብትነትና ፡ ቁጥጥር፡" በሚለው ፡ ከራስል ፡ ኤል ፡ በርማን ፡ በተጻፈው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጾ ፡ ይገኛል ። <u>የኢት ፡ ሕግ ፡ መጽሔት</u> ፡ ፫ኛ ፡ ቮልዩም ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ገጽ ፡ ፭፻፳፭ - ፭፻፶ ።

(ሐ) <u>መሬት ፡ በውል ፡ (በኮንሴሽን) ፡ የመስጠት ፡ ሥልጣን ፤</u>

ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፯(ሠ) ፡ የተሰጠው ፡ በአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝን ፡ መሬት ፡ ለእርሻ ፡ ለኢንዱስትሪ ፡ እና ፡ ለሌላም ፡ ጉዳይ ፡ ማዋል ፡ የሚያስችል ፡ ውል ፡ (ኮንሴሽን) ፡ የመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ ሕጋዊ ፡ እና ፡ ተፈጻሚነትም ፡ ያለው ፡ ነው ። ባለሥልጣኑ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ውሳኔ ፡ የሚሰጠው ፡ ጉዳዩ ፡ ከሚመለከታቸው ፡ ሚኒስቴሮችና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ ወይም ፡ መንግሥት ፡ ለጣለበት ፡ ተግባር ፡ ወኪል ፡ በመሆን ፡ ነው ። የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ተመሳሳይ ፡ ሥልጣን ፡ ጥንቱንም ፡ ያለው ፡ ስለሆነ ፡ ባለሥልጣኑ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ የተሰጠው ፡ አዲስ ፡ ተጨማሪ ፡ ሥልጣን ፡ የለም ።

(፪) <u>ገንዘብ ፡ ነክ ፡ ሥልጣን ፤</u>

እዚህ ፡ ላይ ፡ የምንመረምረው ፡ በቻርተሩ ፡ ተመልክተው ፡ የሚገኙትን ፡ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ነክ ፡ ጉዳዮችን ፡ ነው ።

(ሀ) <u>የአገልግሎት ፡ ዋጋዎችን ፡ ስለመወሰን ፤</u>

የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፯(ለ) ፡ በስሩ ፡ በሚገኘው ፡ ውሀ ፡ መሬትና ፡ እንዲሁም ፡ ሌሎች ፡ መገልገያዎች ፡ ለመጠቀም ፡ የሚከፈለውን ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ ለመወሰን ፡ እንዲችል ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል ።

የ፲፱፻፵፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱ ፡ የሥጋ ፡ ቦርድ ፡ አዋጅ ፡ [39] "ዋጋ" ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ በዚሁ ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ ተወስኖ ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ ሲል ፡ ይተረጉመዋል ። የኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊ ፡ ታሪካዊ ፡ ቅርሶች ፡ አስተዳደር ፡ ትእዛዝም ፡ ለመግቢያ ፡ የሚከፈል ፡ ዋጋን ፡ ጠቅሶ ፡ ይገኛል ። [40] እነዚህን ፡ ሁለቱን ፡ ሕጎች ፡ በመመርኰዝ ፡ "ዋጋ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የሚያመለክተው ፡ ለአንድ ፡ ለተበረከተ ፡ አገልግሎት ፡ ወይም ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ወይም ፡ የመንግሥቱ ፡ ክፍሎች ፡ ለሚያቀርቡት ፡ መገልገያ ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ ነው ፤ ለማለት ፡ ያስደፍራል ።

በዚህም ፡ መሠረት ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ለውሀና ፡ ለሌሎች ፡ እንደግድቦችና ፡ የመስኖ ፡ ውሀ ፡ መተላለፊያ ፡ ቦዮች ፡ ለሚመስሉ ፡ ሁሉ ፡ የመጠቀሚያ ፡ ዋጋ ፡ ወስኖ ፡ የማስከፈል ፡ ሥልጣን ፡ ሕጋዊና ፡ ተፈጻሚነትም ፡ ያለው ፡ ነው ። ቻርተሩ ፡ "ዋጋ" ፡ ሲል ፡ ለተሰጠ ፡ አገልግሎት ፡ ወይም ፡ ተጠቃሚ ፡ ለቀዳው ፡ ውሀ ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ እንጂ ፡ በትክክለኛው ፡ አነጋገር ፡ ግብር ፡ ወይም ፡ ታክስ ፡ ስላልሆነ ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ በቁጥጥሩ ፡ ስር ፡ በሚገኝ ፡ መሬት ፡ የሚጠቀሙትን ፡ ሰዎች ፡ የሚያስከፍለው ፡ ዋጋ ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኝ ፡ የመንግሥት ፡ መሬት ፡ እንደሚከፈል ፡ ኪራይ ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ። ፕሮፌሰር ፡ ፖል ፡ ለሕገ ፡ መንግሥት ፡ ማስተማሪያ ፡ ባዘጋጁት ፡ ጽሑፋቸው ፡ ውስጥ ፡ እንደተገለጠው ፡ ሁሉ ፡ "የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፺፲፫ ፡ የሚመለከተው ፡ ግብርንና ፡ . . . መንግሥትም ፡ በመንግሥትነቱ ፡ ባለው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ሊሰበስባቸው ፡ የሚችል ፡ ክፍያዎችን ፡ እንጂ ፡ . . . አንድ ፡ የግል ፡ ድርጅት ፡ ከሚሰበስባቸው ፡

39. የከብት ፡ ርባታና ፡ የሥጋ ፡ ቦርድ ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ አንቀጽ ፡ ፱(፫) ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፱፻፲፱ ፡ ፳፫ኛ ፡ ዓመት ፡ <u>ነጋሪት ፡ ጋዜጣ</u> ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ።

40. የኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊ ፡ ታሪካዊ ፡ ቅርሶች ፡ አስተዳደርን ፡ ስለማቋቋም ፡ የወጣ ፡ ትእዛዝ ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ አንቀጽ ፡ ፬(፯) ፡ የትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፵፩ ፡ ፳፩ኛ ፡ ዓመት ፡ <u>ነጋሪት ፡ ጋዜጣ</u> ፡ ቁጥር ፡ ፲፯ ።

ክፍያዎች ፡ በዓይነት ፡ የማይለዩትን ፡ አይደለም ። ”[41] የአገልግሎት ፡ ዋጋዎች ፡ መንግሥቱ ፡ ወይም ፡ የመንግሥቱ ፡ ክፍሎች ፡ ለሚያበረክቱት ፡ አገልግሎት ፡ የሚከፈሉ ፡ ክፍያዎች ፡ ናቸው ። ዋጋዎችና ፡ ክፍያዎች ፡ የሚወሰኑት ፡ በአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሲሆን ፡ ይህም ፡ የሚደረገው ፡ በአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ሕግ ፡ ብቻ ፡ በተሰጠ ፡ ሥልጣን ፡ (ለምሳሌ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጥንታውያን ፡ ታሪካዊ ፡ ሀብቶች ፡ አስተዳደር ፡ ትእዛዝን ፡ በሚመስል) ፡ ወይም ፡ በአዋጅ ፡ በተሰጠ፡ ሥልጣን ፡ (ለምሳሌ ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የሥጋ ፡ ቦርድ ፡ አዋጅን ፡ በሚመስል)፡ መሠረት ፡ ሲሆን ፡ የመንግሥት ፡ ወኪል ፡ በመሆን ፡ ለሚቀርብም ፡ አገልግሎት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ስላልን ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ለውሀና ፡ ለሌሎች ፡ መገልገያዎች ፡ ጥቅም ፡ ዋጋ ፡ ሲመድብ ፡ ወሰን ፡ ሊኖርበት ፡ አይገባም ፡ ማለታችን ፡ አይደለም ። የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ባለብቸኛ ፡ መብትን ፡ (ሞኖፖሊስትን ፡) በሚመስል ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ስለሚገኝ ፡ የፈለገውን ፡ ዋጋ ፡ ሊመድብ ፡ ይሞክር ፡ ይሆናል ። እንዲህ ፡ ያለውን ፡ የሥልጣን ፡ መተላለፍ ፡ ሙከራ ፡ ለመቆጣጠር ፡ ባለሥልጣኑ ፡ በደንብ ፡ መልክ ፡ ከማውጣቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ሊያስከፍል ፡ ያቀደውን ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ ሁሉ ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አቅርቦ ፡ እንዲያስፈቅድ ፡ በማድረግ ፡ የመንግሥቱ ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ለሚመደበው ፡ ዋጋ ፡ ሁሉ ፡ ጣራ ፡ ሊያበጅለት ፡ ይገባል ።

ወይም ፡ ደግሞ ፡ ማንኛውም ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ዋጋዎችንና ፡ ክፍያዎችን ፡ በሚወስንበት ፡ ጊዜ ፡ በሥጋ ፡ ቦርድ ፡ አዋጅ ፡ ውስጥ ፡ እንደተመለከተው ፡ ያለ ፡ መመሪያ ፡ እንዲከተል ፡ በማድረግ ፡ በሥልጣኑ ፡ ላይ ፡ ወሰን ፡ ማበጀት ፡ መቻሉን ፡ ደራሲው ፡ ያምንበታል ። ለጉዳዩ ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ የሥጋ ፡ ቦርድ ፡ አዋጅ ፡ ቁጥርም ፡ እንደሚከተለው ፡ በከፊል ፡ ይነበባል ።

> “ቦርዱ ፡ በሚያዘጋጃቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድርጅቶች ፡ ሁሉ ፡ . . . በሚጠቀሙ፡ ሊከፈል ፡ የሚገባውን ፡ ያገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ ለመወሰን ፡ ለማስከፈልና ፡ ለመሰብሰብ ፡ ሆኖም ፡ ያገልግሎቱ ፡ ዋጋ ፡ ለነዚህ ፡ ድርጅቶችና ፡ አገልግሎቶች ፡ መስፋፋት ፡ አጠባበቅና ፡ መሻሻል ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ነገሮች ፡ ለማሟላት ፡ ያህል ፡ እንዲረዳ ፡ በመገመት ፡ ለተጠቃሚዎቹ ፡ የሚሰጠው ፡ አገልግሎት ፡ ከሚፈጀው ፡ የወጪ ፡ ግምት ፡ ጋር ፡ የሚመጣጠን ፡ ሁኖ ፡ በአንድ ፡ ዓይነት ፡ መልክ ፡ መወሰን ፡ አለበት ።”[42]

የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፫ ፡ ዋጋዎችና ፡ ክፍያዎች ፡ ሁሉ ፡ ፓርላማ ፡ በተቀበለው ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ መወሰን ፡ አለባቸው ፡ ባይልም ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ ክፍያ ፡ የመወሰኑ ፡ ሥልጣን ፡ መጀመሪያውኑ ፡ የተሰጠው ፡ በአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ በወጣ ፡ ሕግ ፡ ሳይሆን ፡ የሥጋ ፡ ቦርድ ፡ አዋጅ ፡ ሲወጣ ፡ እንደተደረገው ፡ ሁሉ ፡ እንደአዋጅ ፡ ባለ ፡ መሠረታዊ ፡ ሕግ ፡ ከሆነ ፡ ሕጊትን ፡ ለማስወገድና ፡ የሕዝቡንም ፡ መብት ፡ ይበልጥ ፡ ለማስከበር ፡ እንደሚቻል ፡ ደራሲው ፡ ያምንበታል ።

---

41. ፖል ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቍጥር ፡ ፴፬ ፡ የተጠቀሰው ፡ ገጽ ፡ ፳፬ ።
42. የከብት ፡ ርባታና ፡ የሥጋ ፡ ቦርድ ፡ አዋጅ ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ ፴፱ ፡ የተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ ፫(፲) ።

(ለ) <u>የተሰበሰበውን ፡ ገቢ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለማዋል</u> ፤

የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፮(ለ) ፡ ከውሀ ፡ ከመሬትና ፡ እንዲሁም ፡ ከሌሎች ፡ መገልገያዎች ፡ የሰበሰበውን ፡ ክፍያ ፡ የዲሬክተሮቹ ፡ ቦርድ ፡[43] በሚወስነው ፡ መሠረት ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ለሥራው ፡ ማካሄጃ ፡ ሊያውለው ፡ እንዲችል ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል ።

ባለሥልጣኑ ፡ ተግባሮቹን ፡ በሚያከናውንበት ፡ ጊዜ ፡ የሚሰበስበው ፡ ማናቸውም ፡ ክፍያና ፡ ዋጋ ፡ ሁሉ ፡ ከግብርና ፡ ከታክስ ፡ የተለየ ፡ ቢሆንም ፡ እንደ ፡ መንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ። ግብር ፡ ወይም ፡ ታክስ ፡ የሚጣለው ፡ ለመንግሥት ፡ አገልግሎቶች ፡ ማካሄጃ ፡ ሲሆን ፡ ዋጋዎች ፡ ወይም ፡ ክፍያዎች ፡ የሚጠየቁት ፡ አንድ ፡ የመንግሥት፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፡ ሲያበረክት ፡ ነው ። ቻርተሩ ፡ ራሱ ፡ በቁጥር ፡ ፮(ለ) ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ባለሥልጣኑ ፡ የሚሰበስባቸው ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋዎች ፡ ወይም ፡ ክፍያዎች ፡ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ናቸው ። ምክንያቱም ፡ ከነዚሁ ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋዎች ፡ ውስጥ ፡ ለሥራ ፡ ማካሄጃ ፡ ከሚወጣው ፡ ገንዘብ ፡ የተረፈው ፡ ለመንግሥቱ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ገቢ ፡ እንዲሆን ፡ ቻርተሩ ፡ ያዛልና ።

የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፩ ፡ ግልጥ ፡ በሆነ ፡ አነጋገር ፡ ማናቸውም ፡ የመንግሥት ፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ፡ በሕግ ፡ እንደተፈቀደው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ወጭ ፡ ሊሆን ፡ እንደማይችል ፡ ያዛል ። ስለሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በምንነጋገርበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ "ሕግ" ፡ ስንል ፡ ፓርላማ ፡ መክሮበት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የታወጀ ፡ አዋጅ ፡ ማለታችን ፡ ነው ። ለዚህም ፡ አስተያየት ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፩ ፡ የመጨረሻዎቹ ፡ ቃላት ፡ ድጋፍ ፡ ይሆናሉ ። "<u>ንጉሠ ፡ ነገሥቱ</u> ፡ ... <u>ፓርላሜንቱ ፡ ከተስማማባቸው</u> ፡ <u>በኋላ</u> ፡ ... <u>ሕጎችንም ፡ ድንጋጌዎችንም ፡ ሁሉ ፡ ለማወጅ ፡ መብት ፡ አለው</u> ።" [አንክሮው ፡ የደራሲው ፡ ነው ።] የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፬ም ፡ ለዚህ ፡ አስተያየት ፡ ተጨማሪ ፡ ድጋፍ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፩ ፡ በአዋጅ ፡ የተሰጠ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ ሕግ ፡ አማካይነት ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ የገንዘብ ፡ አወጣጥ ፡ የመቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፡ ሊኖር ፡ አለመቻሉን ፡ በማያከራክር ፡ አኳኋን ፡ ይወስናል ። በሌላ ፡ አነጋገር ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ የገንዘብ ፡ አወጣጥ ፡ ለምሳሌ ፡ ለአንድ ፡ ለተወሰነ ፡ እቅድ ፡ ገንዘብን ፡ ወጭ ፡ ማድረግ ፡ በአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ በወጣ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ ለመምራት ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፪ ፡ ምርኩዝ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ የሚገኘው ፡ ስለገንዘብ ፡ በተለይ ፡ የሚወስነው ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ክፍል ፡ ስለሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ነክ ፡ በሆነ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ከሌላው ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ክፍል ፡ የበላይነት ፡ አለው ። በተጨማሪም ፡ በግልጽ ፡ በተደነገገ ፤ በአዋጅ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የመንግሥትን ፡ ገንዘብ ፡ ወጭ ፡ ለማድረግ ፡ ሥልጣን ፡ መስጠት ፡ አይቻልም ፤ የሚል ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አንቀጽ ፡ እያለ ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፪ ፡ የተመለከተው ፡ የአስፈጻሚውን ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ አቋምና ፡ ተግባር ፡ የመወሰን ፡ ሥልጣንም፡ የመስጠቱ ፡ መብት ፡ የመንግሥትን ፡ ገንዘብ ፡ ወጭ ፡ የማድረግንም ፡ ሥልጣን ፡ ለመስጠት ፡ የሚያስችል ፡ ነው ፤ ለማለት ፡ አይቻልም ።

---

43. አርቃቂው ፡ ደግሞ ፡ ደጋግሞ ፡ በቁጥር ፡ ፲ ፥ ፲፫ ፥ እና ፡ ፲፮ ፡ "ቦርድ ፡ ኦፍ ፡ ኮሚሺነርስ ፥" በሚለው ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ሐረግ ፡ ሲጠቀም ፡ ቆይቶ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ "ቦርድ ፡ ኦፍ ፡ ዲሬክተርስ ፥" በሚለው ፡ መጠቀሙ ካለማስተዋል ፡ ይመስላል ።

ከላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ ምክንያቶች ፡ ሁሉ ፤ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለስልጣን ፡ የሰበሰበውን ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ በቀጥታ ፡ እንዲሠራበት ፡ የማድረጉ ፡ (ለሥራ ፡ ማስኬጃ ፡ የማዋሉ ፡) ሥልጣን ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ሊኖረው ፡ እንዲችል ፡ ተጨማሪ ፡ ሥልጣን ፡ በሌላ ፡ ሕግ ፡ መስጠት ፡ ያሻል ።

(ሐ) <u>ገንዘብ ፡ ስለመበደር ፤</u>

የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ገንዘብ ፡ ለመበደር ፡ እንዲችል ፡ የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፯(ሐ) ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል ።

በዚህ ፡ በተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተው ፡ "ሕጉ" ፡የሚለው ፡ቃል ፡ በቻርተሩ ፡ ውስጥ ፡ ትርጉም ፡ ተሰጥቶት ፡ ስለማይገኝና ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፤ የሚያወጣውንም ፡ ሕግ ፡ ማመልከቱ ፡ ስላልተገለጠ ፡ አስቀድመን ፡ ባቀረብነው ፡ ሀሳብ ፡ መሠረት ፡ "አዋጅ" ፡ ተብሎ ፡ ሊተረጐም ፡ ይገባል ።

በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፹፰ ፡ ወይም ፡ ፹፱ ፡ እና ፡ ፺ ፡ መሠረት ፡ በወጣ ፡ ሕግ ፡ አማካይነት ፡ የመንግሥቱ ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ገንዘብ ፡ መበደር ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፱ ፡ የተፈቀደ ፡ በመሆኑ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ወኪል ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ በሕጉ ፡ ማለት ፡ ፓርላማ ፡ ተቀብሎት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ባወጀው ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ ገንዘብ ፡ የመበደር ፡ ሥልጣን ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የሚስማማና ፡ ተፈጻሚነትም ፡ ያለው ፡ ነው ።

በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፯(ሐ) ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ "ሕጉ" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ የሚያወጣው ፡ ሕግ ፡ ተብሎ ፡ የሚተረጐም ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ ቁጥሩ ፡ (አንቀጹ) ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፱ ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ ስለሚሆን ፡ በአንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ መሠረት ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ የማያገለግል ፡ መባል ፡ ይገባዋል ።

በዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአንቀጽ ፡ ፹፰ ፡ ፹፱ ፡ ወይም ፡ ፺ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ በሚገባ ፡ በቆመው ፡ ሕግ ፡ ካልተፈቀደ ፡ በቀር ፤ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት፡ ግዛት ፡ ውስጥና ፡ በውጭ ፡ አገርም ፡ ቢሆን ፡ በማናቸውም ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ስም ፡ (በአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችም ፡ ጭምር) ፡ ሆኖ ፡ የብድር ፡ ውል፡ መዋዋል ፡ ወይም ፡ ዋስትና ፡ መስጠት ፡ አይቻልም ፤ ሲል ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፱ ፡ ይደነግጋል ። ይህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አንቀጽ ፡ ፓርላሜንቱ መክሮበት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ባወጀው ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ ሥልጣን ፡ ካልተሰጠው ፡ በቀር፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የገንዘብ ፡ መበደር ፡ ሥልጣን ፡ ሊኖረው ፡ እንደማይችል ፡ በማያከራክር ፡ አኳኋን ፡ ይወስናል ።

ባጭሩ ፡ በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፪ ፡ መሠረት ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ስለሆነ ፡ በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፯ (ሐ) ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን፡ መሠረት ፡ ገንዘብ ፡ ሊበደር ፡ የሚችለው ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፱ ፡ የሚወስነው ፡ ተሟልቶ ፡ ሲገኝ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

(መ) <u>በሕዝባዊ ፡ ኩባንያዎች ፡ ገንዘብን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለማዋል ፤</u>

የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ገንዘቡን ፡ (ይህም ፡ በአገልግሎት ፡ ዋጋ ፡ መልክ፡ የተሰበሰበውን ፡ ገንዘብ ፡ የሚጨምር ፡ ይመስላል)፡ጥቅም ፡ በሚያስገኙ ፡ ሕዝባዊ ፡ ኩባንያዎች ፡ ውስጥ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ እንዲችል ፡ የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፯ (ሸ)፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል ።

በ፲፱፻፶፪ቱ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በተቋቋሙት ፡ ሕዝባዊ ፡ ኩባንያዎች ፡ ውስጥ ፡ ገንዘብን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ የመንግሥትን ፡ ገንዘብ ፡ ወጭ ፡ ማድረግ ነው ። ምክንያቱም ፡ ለአንድ ፡ ኩባንያ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ገንዘብ ፡ ወጭ ፡ ለማድ ረግ ፡ በቁጥጥር ፡ ስር ፡ ካለ ፡ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ መውሰድ ፡ ያስፈልጋል ። ይኸን፡ ገንዘብ ፡ ወጭ ፡ ማድረግ ፡ በቀጥታ ፡ ገንዘቡን ፡ ማጥፋት ባይሆንም ፡ ሊያተርፍ ፡ ወይ ም ፡ ሊያከስር ፡ በሚችል ፡ ተግባር ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

በሕዝባዊ ፡ ኩባንያዎች ፡ ውስጥ ፡ ገንዘብን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ "የመንግሥትን፡ ገንዘብ ፡ ወጭ ፡ እንደማድረግ" ፡ ስለሚቆጠር ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፩ ፡ እንደተመለከተው ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የፓርላማ ፡ ፈቃድ ፡ ያስፈልጋል ፤ አለበለዚ ያም ፡ ይህን ፡ ለማድረግ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሥልጣን ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ ከፓርላ ሜንቱ ፡ በአንድነት ፡ ማግኘት ፡ ያሻል ። መንግሥት ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ ኩባንያ ዎች ፡ ላይ ፡ ገንዘቡን ፡ ወጭ ፡ ለማድረግ ፡ ሲያቅድ ፡ በሚያዘጋጀው ፡ በጀት ፡ ውስጥ ፡ ጉዳዩን ፡ ጠቅሶ ፡ ካቀረበ ፡ በኋላ ፡ የፓርላሜንቱን ፡ ፈቃድ ፡ ሊቀበል ፡ የሚገባው ፡ ይመስላል ።[44]

በአዋጅ ፡ ሳይፈቀድለት ፡ ወይም ፡ በፓርላማ ፡ ሥልጣን ፡ ሳይሰጠው ፡ በሕዝ ባዊ ፡ ኩባንያዎች ፡ ገቢውን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲያውል ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥል ጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ሊኖረው ፡ እንዲችል ፡ ቻርተሩ ፡ ሊሻሻል ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ሥልጣን ፡ በሌላ ፡ ሕግ ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባል ።

(ሠ) <u>የዓመት ፡ በጀትን ፡ ስለመፍቀድ ፤</u>

የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፲ ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የዓመት ፡ በጀት ፡ እንደ ሚኖረውና ፡ በባለሥልጣኑም ፡ ስር ፡ ካሉ ፡ ሀብቶች ፡ ማለት ፡ በቁጥር ፡ ፮ (ለ) ፡ መሠ ረት ፡ ከተሰበሰቡ ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋዎችና ፡ ክፍያዎች ፡ ወይም ፡ በቁጥር ፡ ፮ (ሐ) መሠረት ፡ ከተገኘ ፡ የብድር ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ በቁጥር ፡ ፮ (ረ) ፡ መሠረት ፡ ከተገኘ፡ በዓይነት ፡ ከሚሰጥ ፡ ብድር ፡ (ክሬዲት) ፡ የሚገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ ለማድረግ ፡ ባጀ ቱ ፡ በቦርዱ ፡ መጽደቅ ፡ እንደሚገባው ፡ ይወስናል ። ይህም ፡ ማለት ፡ በባለሥልጣኑ ፡ ስር ፡ ካሉ ፡ ሀብቶች ፡ የተገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ የሚይዘው ፡ የበጀቱ ፡ ክፍል ፡ በቦርዱ ፡ ከጸደቀ ፡ በኋላ ፡ የሚጸና ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ቀደም ፡ ብለን ፡ ባቀረብነው ፡ ክርክር ፡ መሠረት ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን፡ ገቢ ፡ በሙሉ ፡ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ ከተሰበሰበው ፡ ገቢ ፡ ማንኛ ውም ፡ ቢሆን ፡ በፓርላማ ፡ ተመክሮበት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ባወጀው ፡ አዋጅ ፡ ካልተ ፈቀደ ፡ በቀር ፡ ወጭ ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ። በቻርተሩ ፡ በተለይም ፡ በቁጥር ፡ ፲ ፡ በግልጥ ፡ እንደተመለከተው ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአንቀጽ ፡ ፻፲፩ ፡ ፻፲፫ ፡ እና ፡ ፻፲፮ ፡ መሠረት ፡ በበጀት ፡ መልክ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ መፈቀድ ፡ ያለበት ፡ ገንዘብ ፡ ከአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ገቢ ፡ ያልተሸፈነው ፡ የበጀቱ ፡ ክፍል ፡ ብቻ ነው ።

በአዋጁ ፡ መሠረት ፡ ሥልጣን ፡ ሳይሰጥ ፡ በገቢው ፡ እንዲጠቀምና ፡ በጀቱንም ፡ በየዓ መቱ ፡ እንዲወስን ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሥልጣን ፡ የሰጠው ፡ የቻርተሩ ፡ ቁጥር፡ ፲ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፩ ፡ ስለሚተላለፍ ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ የለ

---

44. የበጀት ፡ አዋጅ ፡ ፩ሺ፱፻፶፬ ፡ ካፒታል ፡ ወጪዎች ፡ አርእስት ፡ ፬(፳) ፡ አዋጅ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱፻፴፱ ፡ ፳፫ኛ ፡ ዓመት ፡ <u>ነጋሪት ፡ ጋዜጣ</u> ፡ ቁጥር ፡ ፲፱ ።

ውም ። በሌላ ፡ አነጋገር ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ውስጥ ፡ የተ ዘረዘሩት ፡ መብቶችና ፡ ሥልጣኖች ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ምዕራፍ ፡ ፯ ፡ ውስጥ ፡ የተ መለከቱትን ፡ አንቀጾች ፡ ሊተላለፉ ፡ የማይችሉ ፡ ናቸው ። ስለዚህም ፡ በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፲ ፡ መሠረት ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ሕጋዊ ፡ ተፈጻሚነት ፡ ሊኖረው ፡ እንዲችል ፡ ተጨማሪ ፡ ሥልጣን ፡ በሌላ ፡ ሕግ ፡ እንዲሰጥ ፡ ያስፈልጋል ። በተጨማሪም ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ በተጠቀሰው ፡ ምንጭ ፡ መሠረት ፡ በትክክል ፡ እንደተገለጸው ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ገቢ ፡ የሚያገኘው ፡ ከሚያ ከናውናቸው ፡ እቅዶች ፡ መሆኑ ፡ ብቻ፡ የመንግሥቱን ፡ የበጀት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከመ ከተል ፡ ሊያድነው ፡ አይገባም ።

(ረ) ለቦርዱ ፡ አባሎች ፡ የሚከፈለውን ፡ አበል ፡ ስለመወሰን ፤

የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፳ ፡ የአባሎቹን ፡ አበል ፡ ለመወሰን ፡ እንዲችል ፡ ለቦርዱ ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል ።

ለኮሚሽነሮች ፡ ቦርድ ፡ አባሎች ፡ የሚከፈለው ፡ አበል ፡ መወሰን ፡ ያለበት ፡ በ ጀት ፡ በሚፈቀድበት ፡ ጊዜ ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ክፍል ፡ መሆን ፡ አለበት ። ስለዚህ ፡ በቀደሙት ፡ ገጾች ፡ እንደተገለጸው ፤ ሕግ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ የኮሚሽነሮች ፡ ቦርድ ፡ አበልም ፡ ከሌላው ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የበጀት ፡ ዝርዝሮች ፡ ጋር፡ አብሮ ፡ ሊፈቀድ ፡ ይገባል ።

(ቀ) ፡ ስለባለሥልጣኑ ፡ አቋም ፤

በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ መሠረት ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተሰጡት ፡ ሥልጣኖች ፡ ኃላፊነቶችና ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ሰባት ፡ አባሎችና ፡ ዋናው ፡ ሥራ ፡ አስ ኪያጅ ፡ ለሚገኙበት ፡ የኮሚሺነሮች ፡ ቦርድ ፡ ተሰጥቷል ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ አስቸኳይ ፡ ጉዳይ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ በቦርዱ ፡ ስም ፡ አስ ፈላጊውን ፡ እንዲያደርግና ፡ ውሳኔም ፡ እንዲሰጥ ፡ ለዋናው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የቻ ርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱ (ሠ) ፡ ልዩ ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል ።

ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ አስቸኳይ ፡ ሁኔታ ፡ መኖሩ ፡ የሚ ታወቀውም ፡-

(፩) ዋናው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ በራሱ ፡ አስተያየት ፡ ባንድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ውሳኔ ሳይሰጥ ፡ ቢዘገይ ፡ ወይም ፡ አስፈላጊው ፡ በጊዜው ፡ ሳይደረግ ፡ ቢቀር ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ባለሥልጣን ፡ ሥራ ፡ የሚበላሽ ፡ መስሎ ፡ ሲታየው ።

(፪) ይህንኑ ፡ ጉዳይ ፡ ወዲያው ፡ ለቦርዱ ፡ አቅርቦ ፡ ውሳኔ ፡ እንዲሰጥበት ለማድ ረግ ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ሲረዳው ፡ መሆኑ ፡ ተገልጿል ።

ይህ ፡ የአስቸኳይ ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ ወይም ፡ አለመኖሩ ፡ የሥራ ፡ አስኪያጁን ፡ የግል ፡ አስተያየት ፡ የሚመለከት ፡ ስለሆነ ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ወሰን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሲውል ፡ ጠባብ ፡ ሆኖ ፡ አይገኝም ። አስቸኳይ ፡ ጉዳይ ፡ ተፈጥሯል ፤ በማለት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ከሥልጣን ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ተግባር ፡ ፈጽሞ ፡ ባለሥልጣኑን ፡ ኃላ ፊነት ፡ ላይ ፡ ሊጥለው ፡ ይችላል ።

በተጨማሪም ፡ በቁጥር ፡ ፲፱ (ሠ) ፡ በመጨረሻዎቹ ፡ የእንግሊዝኛውና ፡ የአማ ርኛው ፡ ጽሑፎች ፡ ቃላት ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ ያለ ፡ ይመስላል ። አማርኛው ፡ "ይህ ንንም ፡ ለማድረግ ፡ ቦርዱ ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል ፤" ሲል ፡ እንግሊዝኛው ፡ ግን ፡ "--- እንዲህ ፡ ያሉት ፡ እርምጃዎችና ፡ ውሳኔዎች ፡ በቦርዱ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደተፈጸሙ ፡ ይቆጠራሉ ፤" ይላል ።

የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ የሚለው ፡ ምናልባትም ፡ ቦርዱ ፡ በሚገባ ፡ ባጸደቀው ፡ ቋሚ ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ በአስተያየቱ ፡ በአንድ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የዘገየ ፡ ውሳኔ ፡ መስጠት ፡ ወይም ፡ ዘግይቶ ፡ አስፈላጊውን ፡ ማድረግ ፡ የአዋሽን ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሥራ ፡ የሚያበላሽ ፡ መስሎ ፡ ከታየውና ፡ እንዲሁም ፡ ጉዳዩን ፡ ወዲያውኑ ፡ ለቦርዱ ፡ አቅርቦ ፡ ማስወሰን ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ከተረዳው ፡ በቦርዱ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ አስፈላጊውን ፡ ለማድረግና ፡ ውሳኔም ፡ ለመስጠት ፡ ይችላል ፤ ነው ።

የእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ የሚለው ፡ ግን ፡ ዋናው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የሚያደርገው ፡ ወይም ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ የተከናወነ ፡ ከሆነ ፡ አስቀድሞ ፡ የተሰጠ ፡ የቦርዱ ፡ ልዩ ፡ ውሳኔ ፡ ሳያስፈልግ ፡ በቦርዱ ፡ ሥልጣን ፡ እንደተፈጸመ ፡ ይቆጠራል ፤ ነው ።

በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱(ሠ) ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ እንደተመለከተው ፡ ያለ ፡ እንዲህ ፡ ያልተወሰነና ፡ በግልጽ ፡ ያልተዘረዘረ ፡ ሥልጣን ፡ ለዋናው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ መስጠት ፡ "ለአዋሽ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተሰጡት ፡ ኃላፊነቶችና ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ... ለኮሚሽነሮች ፡ ቦርድ ፡ ተሰጥቷል ፤" ከሚለው ፡ ከቻርተሩ ፡ (አንቀጽ ): ፲፫ ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ስለተፈጠረ ፡ የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ትክክለኛ ፡ አስተያየትን ፡ የተከተለ ፡ በመሆኑ ፡ ሊጸናና ፡ ሊከበር ፡ ይገባል ። በሕገ ፡ መንግሥቱም ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፭ ፡ መሠረት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ መደበኛ ፡ (ኦፊሲዬል) ፡ ቋንቋ ፡ አማርኛ ፡ ስለሆነ ፡ በአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ በቁጥር ፡ ፲፱(ሠ) ፡ የተመለከተው ፡ የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ እንደእውነተኛው ፡ የሕግ ፡ አውጭው ፡ ክፍል ፡ አሳብ ፡ ተቆጥሮ ፡ ከእንግሊዝኛው ፡ ይልቅ ፡ የሚጸና ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ።

እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ልዩ ፡ ሥልጣን ፡ ለዋናው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ መስጠት ፡ ራሱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከሚሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ በመተላለፍ፡ እንደተሰጠ ፡ ሥልጣን ፡ የሚቆጠር ፡ ባይሆንም ፡ የተጠቀሰው ፡ ቁጥር ፡ ተብራርቶ ፡ ሥልጣን ፡ አስቀድሞ ፡ መስጠት ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ያደረገው ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ የፈጸመው ፡ ጉዳይ ፡ ለቦርዱ ፡ ቀርቦ ፡ እንዲጸድቅ ፡ ማድረግ ፡ ሕጋዊ ፡ ግዴታ ፡ መሆኑ ፡ እንዲጠቀስና ፡ በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ እና ፡ ፲፱(ሠ) ፡ መካከል ፡ የሚታየው፡ አለመስማማትም ፡ እንዲወገድ ፡ ማድረግ ፡ ይገባል ።

## *መደምደሚያ* ።

ይህ ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ና ፡ የሌሎችም ፡ አግባብ ፡ ያላቸው ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጾችና ፡ የ፲፱፻፶፪ቱ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቁጥሮች ፡ ጠቅላላ ፡ ምርምር ፡ የሚከተሉትን ፡ ፍሬ ፡ ነገሮችና ፡ የሕግ ፡ አስተያየቶች ፡ ይገልጣል ።

ሀ. ጠቅላላ ፡ አስተያየት ፤

(፩) ስለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፤

ሀ/ ስለቻርተሩ ፡ ፎርም ፤

፩/ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፺ ፡ መሠረት ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ በሚያውጀው ፡ ሕግ ፡ ሊወጡ ፡ የሚችሉ ትንና፡የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ቃል ፡ በመከተል፡በአንቀጽ ፡ ፹፰፡እስከ፡፺፡ባለው ፡ መሠረት፡ በወጣ ፡ አዋጅ ፡ ወይም ፡ በአንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ መሠረት ፡ በወጣ ፡ ድንጋጌ ፡ ሊወጡ ፡ የሚ ገባቸውን ፡ ነገሮች ፡ አጣምሮ ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ።

፪/ እንደአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ያለ ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ የሚተዳደር ፡ ባለሥልጣንን ፡ ለማቋቋም ፡ ተገቢ ፡ የሆነው ፡ ሕጋዊ ፡ ፎርም ፡ ከመንግሥት ፡ ማስታ ወቂያ ፡ ይልቅ ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ።

፫/ ቻርተሩ ፡ የወጣበትን ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ሥልጣን ፡ አለመጥቀሱ ፡ "በም ን ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ይሆን ፡ የወጣው ?" ለሚል ፡ ጥያቄ ፡ መነሻ ፡ ስለሚሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ምናልባትም ፡ ጥቅማቸው ፡ የተነካ ፡ ወገኖች ፡ ቻርተሩ ፡ በወጣበት ፡ ሥልጣን ፡ ላይ ፡ መቃወሚያ ፡ ቢያቀርቡላቸው ፡ በየጉዳዩ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ችግር ፡ ይገጥማቸው ፡ ይሆናል ።

አስቀድሞ ፡ እንደተገለጠው ፡ ፎርሙ ፡ ትእዛዝ ፡ ሳይሆን ፡ የመንግሥት ፡ ማስታ ወቂያ ፡ ቢሆንም ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ አንቀጽ ፡ ፳፺ም ፡ ባይጠቅስም ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ የወጣው ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በአን ቀጽ ፡ ፳፺ ፡ ውስጥ ፡ በተመለከተው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ይመስላል ።

ለ/ በቻርተሩ ፡ ስለተመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፤

፩/ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ከተሰጡት ፡ ሥልጣኖችና ፡ ኃላፊነቶች ፡ ጥቂቶቹ ፡ በተለይም ፡ በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፩(ቀ) ፡ ፯(ለ) ፡ እና ፡ (ሸ) ፡ እና ፡ ፲ ፡ የተመለ ከቱት ፡ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ጉዳዮችን ፡ የመቆጣጠር ፡ ሥልጣን ፤ እና ፡ በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፯(መ) ፡ ስር ፡ የተመለከተው ፡ በቁጥጥሩ ፡ ስር ፡ የሚገኙ ፡ የግል ፡ መሬቶችን ፡ የሚመለከት ፡ ደንብ ፡ የማውጣት ፡ ሥልጣን ፡ ተፈጻሚነት ፡ እንዲኖራቸው ፡ ተጨማሪ ፡ ሥልጣን ፡ በሌላ ፡ ሕግ ፡ ሊሰጥ ፡ ይገባል ።

የቻርተሩን ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ ፯(ሐ)ና ፡ (ሠ) ፡ እና ፡ ቁጥር ፡ ፺ን ፡ ፓርላማ ፡ ሊቀበልና ፡ ሊያጸድቃቸውም ፡ ይገባል ፤ ሲሉ ፡ ሚስተር ፡ በርማን ፡[45] የተባሉ ፡ ሕግ ፡ አዋቂ ፡ በጽሑፋቸው ፡ ውስጥ ፡ ገልጠዋል ። ይህን ፡ አስተያየት ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ደራሲ ፡ በሚከተሉት ፡ ምክንያቶች ፡ አይቀበለውም ።

(ሀ) የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፫ ፡ "በልዩ ፡ ሥልጣን" ፡ "ወደ ፡ አዋሽ ፡ ወንዝ ፡ የሚ ገቡትን ፡ ጅረቶችንና ፡ የውሀውን ፡ መፍሰስ ፡ ለመቆጣጠርና ፡ ለመመለስ---" የሚሉ ፡ ጠንካራ ፡ ቃላትን ፡ ይዞ ፡ ቢገኝም ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ልዩ ፡ ሥልጣን ፡ ለመስጠት ፡ ሳይሆን ፡ ሌሎቹ ፡ የቻርተሩ ፡ ቁጥሮች ፡ የሚሰጡትን ፡ ሥልጣን ፡ ባለሥ ልጣኑ ፡ የሚጠቀምበትን ፡ በስሩ ፡ የሚተዳደረውን ፡ ቀበሌ ፡ ዳር ፡ ድምበሩን ፡ ለመወ ሰን ፡ ነው ።

45. ራሰል ፡ ኤል ፡ በርማን ፡ ከላይ ፡ በማስታወሻ ፡ ቁጥር ፡ 38 ፡ የተጠቀሰ ፡

(ለ) አስቀድመን ፡ እንደገለጽነው ፡ ሁሉ ፡ የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፯ (ሐ) ፡ ባለሥልጣኑ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ሕጋዊ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ድርጅት ፡ በመሆን ፡ ሊገባ ፡ የሚፈልገውን ፡ የብድር ፡ ውል ፡ ሁሉ ፡ ሕጉ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ ሊፈጽም ፡ እንደሚችል ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጥ ፡ እንጂ ፡ በጠቅላላው ፡ የመበደር ፡ ሥልጣን ፡ አይሰጠውም ። ይህም ፡ የሚታየው ፡ ቁጥሩ ፡ ራሱ ፡ "በሕጉ ፡ መሠረት ፡" የሚል ፡ ቃል ፡ ይዞ ፡ ስለሚገኝና ፡ የዚህም ፡ ትርጉሙ ፡ ፓርላማ ፡ የተቀበለው ፡ ሕግ ፡ በመሆኑ ፡ ነው ። ቻርተሩ ፡ ራሱ ፡ "በሕጉ" ፡ መሠረት ፡ እንዲፈጸም ፡ ሲያዝ ፡ ለዚያው ፡ ጉዳይ ፡ የፓርላማን ፡ ፈቃድ ፡ ደግሞ ፡ መቀበል ፡ ምንም ፡ የሚጨምረው ፡ ነገር፡ የለም ።

(ሐ) የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፯(ሠ) ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የሚሰጠው ፡ ተጨማሪ ፡ ሥልጣን ፡ ሳይኖር ፡ ባለሥልጣኑ ፡ የመንግሥት ፡ ወኪል ፡ በመሆን፡ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ፡ የመንግሥት ፡ ሚኒስቴሮችና ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ በአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ሥልጣን ፡ ሊጠቀም ፡ መቻሉን ፡ ይደነግጋል ።መሬት ፡ በውል ፡ (በኮንሴሽን) ፡ የመስጠት ፡ ሥልጣን ፡ በመሠረቱ ፡ የመንግሥቱ ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ሥልጣን ፡ ሲሆን ፡ ይህንኑ ፡ ሥልጣን ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን፡ ለመስጠት ፡ የፓርላማ ፡ ፈቃድ ፡ አያሻም ።

(መ) በመጨረሻም ፡ ለሚኒስቴሮች ፡ እና ፡ ለሌሎች ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ በወጣ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የተሰጠውን ፡ ሥልጣን ፤ የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ያስተላልፋል ። አሁንም ፡ ቢሆን ፡ የመሬትን ፡ ባለቤትነት ፡ ሁኔታ ፡ የማጣራትና[46] ፡ በአንድ ፡ ቀበሌ ፡ የሚገኘውን ፡ የመንግሥት ፡ መሬት[47] ፡ ሁሉ ፡ ለማስተዳደር ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሥልጣን ፡ መስጠት ፡ በመንግሥቱ ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ የሚፈጸም ፡ ተግባር ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ የመሬትን ፡ ባለቤትነት ፡ ለማጣራትና ፡ በአዋሽ ፡ ቀበሌም ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ የመንግሥት ፡ መሬት ፡ ለማስተዳደር ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሥልጣን ፡ ለመስጠት ፡ የፓርላማ ፡ ፈቃድ ፡ አያሻም[48] ።

---

46. ምንም ፡ እንኳን ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከቍ. ፡ ሺ፭፻፶፫ - ሺ፮፻፵፯ ፡ ሥር ፡ የሚገኙት ፡ ንብረትንና ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ በመያዣነት፡ መስጠትን ፡ የሚመለከቱት፡ ድንጋጌዎች ፡ በቁጥር ፡ ፫ሺ፫፻፶፫፡ መሠረት ፡ ለጊዜው ፡ እንዳይሠራባቸው ፡ ቢደረግም ፡ የዚሁ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ሺ፭፻፶፬ ፡ የመሬትን ፡ ባለሀብትነት ፡ የማረጋገጥንና ፡ ይህንንም ፡ የመመዝገብን ፡ ኃላፊነት ፡ ለእርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ ይሰጠዋል ።የቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፯ ፡ ዓላማ ፤ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አስረኛው ፡ አርእስት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በሚውልበት ፡ ጊዜ ፡ የአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ በቁጥር ፡ ሺ፭፻፶፫ ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ በቁጥጥሩ፡ ስር ፡ የሚገኙትን ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ መዝገብ ፡ ጠባቂ ፡ ሆኖ ፡ እንደሚይዝና ፡ እና ፡ እስከዚያም ፡ ድረስ ፤ በቍጥር ፡ ፫ሺ፫፻፷፬፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የማይንቀሳቀሱ ፡ ንብረቶችን ፡ ባለሀብትነት ፡ ለማስተላለፍ ፡ ወይም ፡ ለማስቀረት ፡ አግባብ ፡ ባላቸው ፡ የልምድ ፡ ደንቦች ፡ በመገልገል ፡ የሌሎች ፡ የመንግሥት ፡ ሚኒስቴሮች ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ወኪል ፡ በመሆን ፡ ተግባሩን ፡ እንደሚያከናውን ፡ ለማመልከት ፡ ነው ።

47. እንዲሁም ፡ በሌላ ፡ ተመሳሳይ ፡ ትእዛዝ ፡ ሥልጣኑ ፡ ለሌላ ፡ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በሕግ ፡ መንገድ ፡ ካልተሰጠ ፡ በስተቀር ፡ የመንግሥት ፡ የሆኑ ፡ መሬቶችን ፡ ሁሉ ፡ የማስተዳደሩ ፡ ሥልጣን ፡ ለመሬት ፡ ይዞታና ፡ አስተዳደር ፡ ሚኒስቴር ፡ ተሰጥቷል ። ስለሚኒስትሮች ፡ (የሚኒስትሮች ፡ ተግባርና ፡ ሥልጣን)፡(ማሻሻያ ፡ ቁጥር ፡ ፱) ፡ ትእዛዝ ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ (ሐ) ። ትእዛዝ ፡ ቁጥር ፡ ፵፯ ፡ ፳፭ኛ ፡ ዓመት ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቁጥር ፡ ፳፫ን ፡ ይመለከቷል ።

48. ከዚያው ፤ የትእዛዙ ፡ ቁጥር ፡ ፲፰(ሐ)-(ሸ) ፡ የመንግሥት ፡ የሆኑ ፡ መሬቶችን ፡ የማስተዳደር ፡ የመሸጥ ፡ የማከፋፈል ፡ ሥልጣን ፡ መሬት ፡ የሚመዘገብበትን ፡ ሁኔታ ፡ የመወሰን ፡ መዝገቡም ፡ በደንብ ፡ መያዙን ፡ የማረጋገጥና ፡ በተጨማሪም ፡ ስለ ፡ መሬት ፡ ይዞታ ፡ የሚነሱትን ፡ በባለቤትነት ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ክርክሮች ፡ ሁሉ ፡ በተፋጠነ ፡ ሁኔታ ፡ ውሳኔ ፡ እንዲያገኙ ፡ አስፈላጊውን ፡ እርምጃ ፡ የመውሰዱን ፡ ኃላፊነት ፡ ለመሬት ፡ ይዞታና ፡ አስተዳደር ፡ ሚኒስቴር ፡ ይሰጠዋል ።

በነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ምክንያቶች ፡ የዚህ ፡ ምርምር ፡ ድርሰት ፡ ደራሲ ፡ ከላይ ፡ የተ ጠቀሱት ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተሰጡት ፡ ሥልጣኖች ፡ በፓርላማ ፡ መፈቀድና ፡ መጽደቅም ፡ ይገባቸዋል ፤ ለሚለው ፡ አስተያየት ፡ ሕጋዊ፡ ድጋፍ ፡ ያለ ፡ መስሎ ፡ አይታየውም ።

፪/ በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱ (ሠ) ፡ ስር ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ ዋና ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የተሰጡት ፡ የተለዩ ፡ ሥልጣኖች ፡ በዝርዝር ፡ ካልተገለጡ ፡ በቀር ፡ በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፲፫ ፡ ስር ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የኮሚሽነሮች ፡ ቦርድ ፡ ከተሰጡት ፡ ሥልጣኖች ፡ ኃላፊነቶችና ፡ ተግባሮች ፡ ጋር ፡ እጅግ ፡ የሚመሳ ስሉ ፡ ናቸው ። ስለዚህም ፡ በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፲፱ (ሠ) ፡ ስር ፡ የተመለከተው ፡ አስቸ ኳይ ፡ ሁኔታ ፡ በሚኖርበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ዋናው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ በቦርዱ ፡ ስም ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠትና ፡ አስፈላጊውንም ፡ ለማድረግ ፡ እንዲችል ፡ አስፈላጊው ፡ የቦ ርዱ ፡ ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡ እንደተሰጠው ፡ ቦርዱ ፡ አስቀድሞ ፡ በሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፡ ሥልጣን ፡ እንዳስተላለፈለት ፡ ማመልከት ፡ ይገባዋል ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ በአንደኛው ፡ ተራ ፡ ቁጥር ፡ ውስጥ ፡ የተገለጹት ፡ ለባ ለሥልጣኑ ፡ በመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ መልክ ፡ የተሰጡት ፡ ሥልጣኖች ፡ በመ ሠረታዊ ፡ ሕግ ፡ እንጂ ፡ የአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ በሚያወጣው ፡ ሕግ ፡ ሊሰጡ ፡ የሚገባቸው ፡ ስላልሆኑ ፡ የተባሉትን ፡ ሥልጣኖች ፡ ፓርላማው ፡ ተስማምቶበት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ባጸደቁት ፡ አዋጅ ፡ እንደገና ፡ በማሳወጅ ፡ ሕጋዊ ፡ ጉድለቱን ፡ ለማ ሟላት ፡ ይቻላል ።

በሁለተኛው ፡ ተራ ፡ ቁጥር ፡ የተመለከተው ፡ በውስጣዊ ፡ አቋም ፡ ረገድ ፡ የሚ ታየው ፡ ጉድለት ፡ ማለት ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣንና ፡ ለቦርዱ ፡ ሥራ ፡ አስኪ ያጅ ፡ በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፲፫ ፡ እና ፡ ፲፱(ሠ) ፡ የተሰጡት ፡ ሥልጣኖች ፡ አለመስማ ማት ፡ ግን ፡ ሊወገድ ፡ የሚችለው ፡ የቁጥር ፡ ፲፱(ሠ)ን ፡ ቃል ፡ በማብራራትና ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁም ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔና ፡ የሚያደርገውም ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የተ ፈቀደ ፡ ወይም ፡ በኋላ ፡ ለቦርዱ ፡ ቀርቦ ፡ የሚጸድቅ ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

፪/ <u>ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ሥልጣን ፤</u>

(ሀ) <u>የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፤</u>

፩/ አስቀድሞ ፡ እንደተገለጸው ፡ ሁሉ ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ በእንግሊዝኛውና ፡ በአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ መካከል ፡ በመሠረቱ ፡ የቃል ፡ መለያየት ፡ አለ ።

፪/ ይህም ፡ የቃል ፡ መለያየት ፡ ሊፈጠር ፡ የቻለው ፡ በሕግ ፡ አውጭው ፡ ታስቦ ፡ የተደረገ ፡ ሳይሆን ፡ አንቀጹ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ሲተረጐም ፡ ተገቢው ፡ ጥንቃቄ ፡ ባለ መደረጉ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ የተሟላ ፡ ሆኖ ፡ እንዲገኝ ፡ በእን ግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ሊደገፍ ፡ ይገባል ።

፫/ አንቀጽ ፡ ፳፯ን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ በወጣ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠ ረት ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚሰጥ ፡ ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡ ውስጣዊ ፡ አቋምን ፡ ተግባር ፡ መወሰንን ፡ እና ፡ (፩) የመቆጣጠርን ፡ (፪) የፖሊስ - መስልን ፡ እና ፡ (፫) የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ጉዳይን ፡ መቆጣጠርን ፡ የማይመስል ፡ ሥልጣን ፡ መስጠትን ፡ የሚመለከት ፡ መሆን ፡ አለበት ።

ለ/ ሌሎች ፡ አንቀጾች ፤

በአንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ መሠረት ፡ ሊሰጡ ፡ የማይችሉትን ፡ ከላይ ፡ በተራ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ሥልጣኖች ፡ ለአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ለመስጠት ፡ የተፈለገ ፡ ከሆነ ፡ በሌሎች ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጾች ፡ በተለይም ፡ በአንቀጽ ፡ ፹፰ ፡ ፹፱ ፡ ወይም ፡ ፺ ፡ መሠረት ፡ መሰጠት ፡ አለባቸው ።

ሐ/ አሳብ ፤

፩/ በመሠረቱ ፤ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ መቋቋም ፡ የሚገባቸው ፡ በትእዛዝ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ይህም ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፳፯ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በአስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ሥልጣን ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ዋናው ፡ የሕግ ፡ ዓይነት ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ያለውም ፡ ትእዛዝ ፡ ሲቋቋም ፡ የታቀደውን የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጣዊ ፡ አቋም ፡ የሚመለከት ፡ ተራ ፡ ሥልጣን ፡ የሚሰጥና ፡ ተግባርም ፡ የሚወስን ፡ መሆን ፡ ሲገባው ፡ ሊሰጥ ፡ የታቀደ ፡ የመቆጣጠር ፡ የፖሊስ ፡ መሰል ፡ እና ፡ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ነክ ፡ ጉዳዮችን ፡ የመቆጣጠር፡ ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡ በአዋጅ ፡ ወይም ፡ በድንጋጌ ፡ ሊሰጥ ፡ ይገባል ።

፪/ አንድ ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ በሚወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ክርክር ፡ ተነስቶ ፡ ጉዳዩ ፡ ቢቀርብላቸው ፡ አይተው ፡ መወሰን ፡ ይቻላቸው ፡ ዘንድ ፡ የወጣበት ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ሥልጣን ፡ በውስጡ ፡ ሊገለጥ ፡ ይገባል ።

፫/ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሊያስከፍሉ ፡ ያቀዱትን ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋና ፡ ክፍያ ፡ ሁሉ ፡ አስቀድመው ፡ ለሚኒስቴሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አቅርበው እንዲያስፈቅዱ ፡ በማድረግ ፡ የአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ በዋጋውና ፡ በክፍያው ፡ ላይ ፡ ሌላው ፡ ቢቀር ፡ ጣራ ፡ ሊያበጅለት ፡ ካልሆነም ፡ ደግሞ ፡ በሥጋ ፡ ቦርድ ፡ አዋጅ ፡ (፪፻፲፪/፶፯) ፤ በቁጥር ፡ ፫(፲) ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተውን ፡ መመሪያ ፡ የተባሉት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ እንዲከተሉ ፡ ማድረግ ፡ ይገባዋል ።

፬/ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፫ ፡ የአገልግሎት ፡ ዋጋዎችና ፡ ክፍያዎች ፡ ሁሉ ፡ በፓርላማ ፡ በጸደቀ ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ እንዲወሰኑ ፡ ባያዝም ፡ ዋጋዎችንና ፡ ክፍያዎችን ፡ የመወሰኑን ፡ ሥልጣን ፡ መጀመሪያውኑ ፡ በእንዲህ ፡ ያለው ሕግ ፡ (በአዋጅ) ፡ መስጠቱ ፡ ኃሜትን ፡ ከማስወገዱም ፡ በላይ ፡ የሕዝቡን ፡ መብት ፡ በሚገባ ፡ ለመጠበቅ ፡ ያስችላል ።

፭/ በቻርተሩ ፡ ቁጥር ፡ ፬(ሸ) ፡ ፯ (ለ) ፡ (መ) ፡ እና (ቀ) እንደዚሁም ፡ ፲ ፡ እና ፡ ፳ ፡ ለአዋሽ ፡ ሸለቆ ፡ ባለሥልጣን ፡ የተሰጡት ፡ ሥልጣኖች ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከአንቀጽ ፡ ፹፰፡ እስከ፡ ፺ ፡ በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ በወጣ ፡ አዋጅ ፡ መሰጠት ፡ ስለሚገባቸው ፡ ቻርተሩ ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ መሻሻል ፡ አለበት ። የቀሩት ፡ በቻርተሩ ፡ ውስጥ፡ የተመለከቱት ፡ ቁጥሮች ፡ ግን ፡ በበለጠ ፡ በመብራራት ፡ በትእዛዝ ፡ መልክ ፡ ሊወጡ ፡ ይችላሉ ።